# የረመዳን ወር ሕግጋትን የተመለከቱ 100 ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

በተጨማሪም

## የዘካተል ፊጥር ህግጋቶች ባጭሩ ተካተውበታል

*አዘጋጅ፡- አቡ ዐብድረሕማን ዐብደላህ ቢን አሕመድ አል-ኢርያኒ*

ተርጓሚ፡- ኻሊድ ጠይብ (አቡ ዐብድልመናን)

@All Rights
Reserved

Adress

Mob. 0910345523

E-mail:
abuhiba2003@gmail.com

Addis Ababa, Ethiopia

የመጀመሪያ እትም

መጋቢት2011

# ማውጫ

ማውጫ……………………………………………………………...2
መግቢያ……………………………………………………….............6
ጥ1. የረመዳን ፆም ምንድን ነው?……………………………...........7
ጥ2. የረመዳን ወር ፆም የተደነገገው መቼ ነው?………………......7
ጥ3. የረመዳን ፆም ግዴታ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው?……......7
ጥ4. ሶላት የማይሰግድ ሰው ፆሙ ተቀባይነት አለውን?……………....9
ጥ5. የረመዳንን ወር መፆም ግዴታ የሚሆነው መቼ ነው?…………..10
ጥ6. የረመዳን ወር ጨረቃ ካልታየ ምን ማድረግ አለብን?………......11
ጥ7. አጠራጣሪ የሆነን ቀን መፆም ፍርዱ ምንድን ነው?……...........11
ጥ8. ረመዳን አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው የሱና ፆም መፆም ይቻላልን?…………………………………………………………………11
ጥ9. ይህ ክልከላ ሱና የመፆም ልምድ ያለውን ሰው ያካትታልን?.......12
ጥ10. ክልከላው ቀዷ የሚያወጣን ሰው ይካትታልን?………………….12
ጥ11. ክልከላው የስለት ፆም የሚፆምን ሰው ያክትታልን?…….........12
ጥ12. የረመዳን ወር ጨረቃን ሁሉም ሰው ማየት አለበትን?……….....13
ጥ13. የረመዳን ወር ጨረቃን ለማየት የአንድ ሰው ምስክርነት ይበቃልን?…………………………………………………………......13
ጥ14. የአንድ አገር ሰዎች ጨረቃን ካዩ የሌላ አገር ሰዎች መፆም ግድ ይላቸዋልን?………………………………………………………...14
ጥ15. የረመዳንን ወር መፆም ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?......14
ጥ16. ህፃናት በመፆም ይገደዳሉን?……………………………………16
ጥ17. የወር አበባዋ ከፈጅር በፊት የቆመላት ሴት ከፈጅር በኃላ ብትታጠብ መፆም ግዴታ ይሆንባታልን?……………………………16
ጥ18. ፆመኛ ሆና ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የወር አበባ የመጣባት ሴት ምን ማድረግ አለባት?…………………………………….............16
ጥ19. ለህመምተኛ መፆም ይፈቀድለታልን?…………………………...17
ጥ20. የፀነሰች ሴት እና የምታጠባ እናት ፍርዳቸው ምንድን ነው?.....17
ጥ21. አንዲት ሴት በረመዳን የወር አበባን የሚያስቀር መድሐኒት መጠቀም ትችላለችን?……………………………………………......17
ጥ22. በእርጅና ምክንያት መፆም ያልቻለ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?...18
ጥ23. የመዳን ተስፋ የሌለው ህመምተኛ ፍርዱ ምንድን ነው?……....18
ጥ24. ዘወትር መድሐኒት የሚጠቀም ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?........18
ጥ25. እየፆመ በመርፌ መድሐኒት የሚጠቀም ሰው ፍርዱ ምንድን

ነው?......................................................................19
ጥ26. ከተለምዶዋ ውጭ ደም የፈሰሳት ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?.....19
ጥ27. ያመኛ ሆና ፅንስ ያስወረዳት ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?..........19
ጥ28. በረመዳን ከአርባ ቀን በፊት የውልደት ደሟ የቆመላት ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?...................................................................20
ጥ29. የረመዳን ወር መፃም የሚጀመረው መቼ ነው?..................20
ጥ30. የእውነተኛው ጎህ ምልክት ምንድን ነው?........................21
ጥ31. ጎህ ሳይቀድ ለጥንቃቄ የፈጅርን አዛን ማቻኮል ይቻላልን?........21
ጥ32. የፈጅርን የመጀመሪያ አዛን በመተው በቁርኣንና በዚክር መቀየር ይቻላልን?....................................................................22
ጥ33. ሌሊቱ ገና መስሎት ከበላና ከጠጣ በኃላ ጎህ የቀደደ መሆኑን ያወቀ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?........................................23
ጥ34. ከፈጅር 2ኛ አዛን በኃላ የሚጠጣ ነገርን የጠጣ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?...................................................................23
ጥ35. ጀናባ ሆኖ ፈጅር የደረሰበት ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?..........24
ጥ36. የጀናባን ትጥበት ጎህ እስኪቀድ ማዘግየት ፍርዱ ምንድነው?....25
ጥ37. በረመዳን ቀን ኢሕቲላም የሆነ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?.......25
ጥ38. ሱሑርን መመገብ ፍርዱ ምንድን ነው?.........................25
ጥ39. ሱሑር መመገብ በረከት አለው ለምን ተባለ?....................26
ጥ40. የሱሑርን በረከት ለማግኘት ምን ያክል መመገብ አለበት?........26
ጥ41. የተሻለና ጥሩ ሱሑር ምንድን ነው?.............................27
ጥ42. ሱሑር ምሳ ተብሎ ይጠራልን?....................................27
ጥ43. ሱሑርን ማዘግየት እንዴት ይታያል?..............................27
ጥ44. ሱሑርን ሳይመገብ የፆመ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?............28
ጥ45. በረመዳን ቀን ያለምንም ምክንያት የበላ ወይም የጠጣ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?...................................................................28
ጥ46. ትንሽ የበላና ብዙ የበላ ሰው ልዩነት አለውን?....................28
ጥ47. ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ፃመኛ ፍርዱ ምንድን ነው?............28
ጥ48. በረመዳን ቀን ፃመኛ ሆኖ ከሚስቱ ጋር ግንኙነት የፈፀመ ፍርዱ ምንድን ነው?...................................................................29
ጥ49. ማድረግ ያለበት ከፋራ (ማካካሻ) ምንድን ነው?..................29
ጥ50. ከፋራ ማድረግ ያልቻለ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?................30
ጥ51. ባሏ የተገናኛት ሴት ከፋራ አለባትን?...............................30
ጥ52. ፃመኛ ሆኖ ሚስቱን ከተገናኘ በኃላ ጉዞ ያደረገ ወይም የታመመ ሰው ከፋራ አለበትን?..................................................30

ጥ53. ባሏ አስገድዷት ግንኙነት የፈፀመች ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?..30
ጥ54. ከፋራ ሲያወጣ ሁሉንም ድሆች በአንድ ላይ በአንድ ቀን ማብላት ግዴታ ነውን?........................................................31
ጥ55. አንድ ሰው ከፋራ ሲያወጣ የ30 ሰው ምግብ ለአንድ ሰው መመገብ ይችላልን?..................................................................31
ጥ56. በዚህ ከፋራ (ማካካሻ) ማጥገብ ግዴታ ነውን?...................31
ጥ57. በዚህ ከፋራ (ማካካሻ) ቴምርን የመሰለ አንድ አይነት ምግብ ማድረግ ይቻላልን?......................................................................31
ጥ58. ፆመኛ ሆኖ ሚስቱን ተገናኝቶ የዘር ፈሳሽ ያልፈሰሰው ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?......................................................................31
ጥ59. በረመዳን ፆም በቀኑ ክፍለ ጊዜ በአንድ ቀን ውስጥ ሚስቱን ደጋግሞ የተገናኘ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?.............................32
ጥ60. ከረመዳን ቀናቶች ውስጥ ሁለት ቀን ሚስቱን የተገናኘ ስንት ከፋራ አለበት?...........................................................................32
ጥ61. በአውሮፕላን የሚጓዝ ሰው ማፍጠር ይችላልን?.................32
ጥ62. ጉዞን ያሰበ ሰው ከአገሩ ሳይወጣ መብላት ይችላልን?.............32
ጥ63. ለመንገደኛ ሰው ከመፆምና ከማፍጠሩ የትኛው የተሻለ ነው?.....32
ጥ64. ዘወትር በጉዞ ላይ ያለ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?...............32
ጥ65. ፆመኛ ዋግምት ማድረግ ይችላልን?...............................33
ጥ66. ፆመኛ ሆኖ ሚስቱን መሳም ይችላልን?...........................33
ጥ67. ፆመኛ የሆነ ሰው መፋቂያን መጠቀም ይችላልን?.................33
ጥ68. ፆመኛ የሆነ ሰው የጥርስ ሳሙናን መጠቀም ይችላልን?..........34
ጥ69. ፆመኛ ሆኖ ውዱ ሲያደርግ ውሃ ወደ ሆዱ የገባበት ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?...........................................................................34
ጥ70. አንድ ፆመኛ እራሱን ለማቀዝቀዝ ፀጉሩን መታጠብ ይቻላልን?..34
ጥ71. ፆመኛ የሆነ ሰው በቀን ከአንዴ በላይ መታጠብ ይችላልን?.......34
ጥ72. ዐይንን ኩል መኳል ፆምን ያበላሻልን?...........................34
ጥ73. የዐይን፣ የጆሮና የአፍንጫ ጠብታ ፆም ያበላሻልን?...............35
ጥ74. ፆመኛ የሆነ ሰው አቧራና ጭስ ቢገባበት ፆሙ ይበላሻልን?......35
ጥ75. ምራቅን መዋጥ ፆምን ያበላሻልን?..................................35
ጥ76. አክታን መዋጥ ፆምን ያበላሻልን?..................................35
ጥ77. ማስታወክ ፆምን ያበላሻልን?.......................................35
ጥ78. ማቀርሸት ፆምን ያበላሻልን?.......................................36
ጥ79. አንድ ፆመኛ ፆሙን የሚያፈጥረው መቼ ነው?...................36
ጥ80. አፍጥርን ማፍጠን ፍርዱ ምንድን ነው?.........................36

ጥ81. ኮከቦች እስኪታዩ ድረስ አፍጥርን ማዘግየት ፍርዱ ምንድን ነው?....................................................37
ጥ82. አፍጥርን መብላት የተወደደው ከመግሪብ በፊት ነው ወይስ ከመግሪብ በኋላ?....................................................38
ጥ83. ፆመኛ ሰው የሚያፈጥረው በምንድን ነው?........................39
ጥ84. አንድ ፆመኛ ሲያፈጥር የሚለው ዱዓ ምንድን ነው?..............39
ጥ85. ፆመኛን ማስፈጠር ያለው አጅር ምንድን ነው?....................39
ጥ86. አንድ ፆመኛ ተጋብዞ ካፈጠረ በኋላ ለጋባዡ የሚያደርገው ዱዓ ምን ቢሆን ይመረጣል?....................................................40
ጥ87. የዊሳል ትርጉምና ፍርዱ ምንድን ነው?............................40
ጥ88. እስከ ሱሑር ድረስ ሳያፈጥሩ ፆምን መቀጠል ፍርዱ ምንድን ነው?....................................................41
ጥ89. በረመዳን ሌሊት የመስገድ ትሩፋት ምንድን ነው?................41
ጥ90. የረመዳንን የሌሊት ሶላት በአንድ ላይ መስጂድ ውስጥ መስገድ ይቻላልን?....................................................41
ጥ91. የሌሊት ሶላት የሚሰገደው ስንት ረከዓ ነው?......................42
ጥ92. የሌሊት ሶላት እየሰገደ የደከመው ሰው ቁጭ ብሎ መስገድ ይችላልን?....................................................43
ጥ93. ቁጭ የሚለው ሰጋጅ እንዴት ነው የሚሰግደው?..................43
ጥ94. በረመዳን የሌሊት ሶላት ቁኑት ማድረግ ይቻላልን?...............43
ጥ95. ከዚህ ዱዓ ውጭ መጨመር ይቻላልን?............................44
ጥ96. ይህ ቁኑት የሚደረገው ከሩኩዕ በፊት ነው ወይስ በኋላ?.........44
ጥ97. የዊትር ሶላትን ስንጨርስ የሚባል ዚክር አለን?...................45
ጥ98. ለይለተል ቀድር የሚሆነው መቼ ነው?.............................45
ጥ99. ሌሌቱ ለይለተል ቀድር ለመሆኑ ምልክቱ ምንድን ነው?.........46
ጥ100. የተከለከሉ ምስሎችና ሙዚቃን ማዳመጥ የፆምን ምንዳ ይቀንሳልን?....................................................46
ዘካተል ፊጥራችንን በታዘዝነው መልኩ እናውጣ?........................48
ዘካተል ፊጥር ተብሎ የተሰየመው ለምንድን ነው?......................49
ዘካተል ፊጥር የተደነገገው መቼ ነው?.................................49
ዘካተል ፊጥር የተደነገገበት ምክንያት ምንድን ነው?.....................49
ዘካተል ፊጥር ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?........................49
ዘካተል ፊጥርን መስጠት ግዴታ የሚሆነው መቼ ነው?.................50
አንድ ሰው የሚያወጣው የዘካተል ፊጥር መጠን ምን ያህል ነው?.....50
ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ (በብር) ማውጣት ይቻላልን?...................51

# መግቢያ

ከሰማይ በላይ ለሚገኘው አዛኙ ጌታችን ﷲ ምስጋና የተገባ ነው። ሁሉንም የዲን ጉዳዮች አስተምረውን በሄዱት በነብያችን ﷺ ላይ የﷲ ሶላትና ሰላም ይሁን። ጌታችን በተከበረው መፅሐፍ እንዲህ ይላል:-

فَاعْلَمْ أَنَّهُ لا إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَاسْتَغْفِرْ لِذَنبِكَ

***((ከﷲ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እወቅ። ለስህተትህም ምህረትን ጠይቅ))***
***(ሙሐመድ 19)***

ኢማሙ አል ቡኻሪ በሶሒሕ ኪታቡ ውስጥ ይህንን አንቀፅ በመመርኮዝ እውቀት ከየትኛውም ስራም ይሁን ንግግር እንደሚቀድም አስገንዝበዋል። ምክንያቱም ያለ እውቀት የሚሠራ ሥራ ከጥሩው ክፋቱ ይበልጣል። “የጃሂል ዒባዳ ተመልሶ እዳ” እንደተባለው ማለት ነው።

በእስልምና ውስጥ ከተደነገጉት አምልኮቶች ውስጥ አንዱ የረመዳን ፆም ነው። ታዲያ ይህንን ዒባዳ ስንፈፅም ነቢያችንﷺ በሰሩትና በፈፀሙት መልኩ እንዲሆንና ﷲ ም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የእውቀት ሚና ከፍ ያለ ነው። እኔም ይህንን መርሕ አንግቤ ሙስሊም ወንድም እህቶቼን ይጠቅም ዘንድ ፆምን የተመለከቱና በአብዛኛው ጊዜ ሰዎች ላይ ውዥንብር የሚፈጥሩትን ጥያቄዎች ያካተተ ፅሁፍ አቅርቤያለሁ። ይህን ፅሁፍ ሸይኽ ዐብደላህ አል-ኢርያኒ በጥያቄና መልስ ያዘጋጁት ሲሆን እኔም ለአብዛኛው ሙስሊም ይጠቅማል ብዬ ተስፋ በማድረግ ወደ አማርኛ በመተርጎም እንካችሁ ብያለሁ።

በዚህ ፅሁፍ ﷲ ሙስሊሞችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ እለምነዋለሁ።

ተርጓሚው:- ኻሊድ ጠይብ

**دار الحديث بمسجد الفلاح**

ረጀብ 21 1440 ሂ.

*ጥ1. የረመዳን ፆም ምንድን ነው?*

*መ. ፆም ሸሪዓዊ ገለፃው፡- ለየት ያለ መቆጠብ፣ ለየት ባለ ወቅት፣ ለየት ባለ ግለሰብና ለየት ባለ መሥፈርት የሚፈፀም አምልኮት ነው፡፡* فتح الباري, شرح مسلَم

**ለየት ያለ መቆጠብ ማለት**፡- ሸሪዓው ለይቶ ከገለፃቸው ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች መቆጠብ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- መብላት፣ መጠጣት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም፣ ምግብ ነክ የሆኑ መድሐኒቶችን መውሰድ ወ.ዘ.ተ

**ለየት ባለ ወቅት ሲባል**፡- ሸሪዓ ለይቶ በገለፀው ወቅት ሲሆን እርሱም፡- ከእውነተኛው ጎሕ መቅደድ ጀምሮ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ድረስ ይሆናል፡፡

**ለየት ባለ ግለሰብና ለየት ባለ መስፈርት ሲባል**፡- ሙስሊም የሆነ፣ አዕምሮው ጤነኛ የሆነ፣ መፆም የሚችልና አገሩ ላይ ተቀማጭ የሆነ (መንገደኛ ያልሆነ) ሲሆን ፤ ነገር ግን የወር አበባ እና የውልደት ደም ያለባቸው ሴቶችን አያካትትም፤ ላለመፆም ሸሪዓዊ ምክንያት ያለው ሰውም መፆም ግዴታ አይሆንበትም፡፡ ነገር ግን ይህ ምክንያት ከተወገደ በኃላ ቀዷ ያወጣል፡፡

*ጥ2. የረመዳን ወር ፆም የተደነገገው መቼ ነው?*

*መ. ይህ ፆም የተደነገገው በሂጅራ አቆጣጠር በሁለተኛው አመት ሲሆን በሸዕባን ወር ላይ ነውም ተብሏል፡፡ የ ﷲ መልዕክተኛም* ﷺ ዘጠኝ ረመዳኖችን ፆመዋል፡፡

"المجموع" للنووي, "زاد المعاد", "سبل السلام"

*ጥ3. የረመዳን ወር ፆም ግዴታ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው?*

*መ. ማስረጃው የ ﷲ እና የመልዕክተኛው ﷺ ንግግር ሲሆን ﷲ እንዲህ ይላል፡-*

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣﴾البقرة: ١٨٣

***" እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት ህዝቦች ላይ እንደተደነገገው በናንተ ላይም ተደነገገ፡፡ (እርሱን) ልትጠነቀቁት ይከጀላልና፡፡"*** *(አል በቀራህ -183)*

በሌላም አንቀፅ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُ﴾البقرة: ١٨٥

***((ከናንተ ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው፡፡))*** (አል በቀራህ 185)

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ዐብደላህ ቢን ዑመር رضي الله عنهما ባስተላለፉት ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛﷺ እንዲህ ይላሉ፡-

بُنِيَ الإِسْلامُ عَلى خَمْسٍ: شَهادَةِ أَنْ لاَ إِلهَ إِلاَّ اللهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ وَإِقامِ الصَّلاةِ وَإِيتاءَ الزَّكاةِ وَالْحَجِّ وَصَوْمِ رَمَضَانَ. متفق عليه

***"እስልምና በአምስት ነገሮች ተገንብቷል፡፡ ከﷲ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም ሙሐመድም ﷺ የ ﷲ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር፣ ሶላትን መስገድ፣ ዘካን መስጠት፣ የረመዳንን ወር መፆም እና ሐጅን ማድረግ"*** ናቸው፡፡

በሌላም ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ጦልሐ ቢን ዑበይዱላህ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ አንድ የገጠር ሰው የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ ዘንድ በመምጣት ﷲ ግዴታ ስላደረጋቸው አምልኮቶች ጠየቃቸው። ከጠየቃቸው ጥያቄዎች ውስጥ ስለ ረመዳን ወር ፆም ነበር። እርሳቸውም ﷺ እንዲህ አሉት፦

« شَهْرَ رَمَضَانَ ، إِلاَّ أَنْ تَطَّوَّعَ شَيْئًا » متفق عليه

*"ከፆም ግዴታ የሆነብህ የረመዳንን ወር መፆም ነው።"*

-ብዙ ዑለማዎች የረመዳን ወር መፆም ግዴታ በመሆኑ ላይ የዑለማዎችን ስምምነት የገለፁ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ ኢማሙ አን-ነወዊ (مجموع) የሚባለው ኪታባቸው ላይ አስፍረዋል።

*ጥ4. ሶላት የማይሰግድ ሰው ፆሙን ﷲ ይቀበለዋልን?*

*መ. የእውቀት ባልተቤቶች እንዳሉት ﷲ ሶላት የማይሰግድ ሰውን ፆም አይቀበለውም። ﷲ እንዲህ ይላል፦*

﴿ إِنَّمَا يَتَقَبَّلُ ٱللَّهُ مِنَ ٱلْمُتَّقِينَ ﴾المائدة: ٢٧

***((ﷲ እኮ የሚቀበለው ከጥንቁቆቹ ብቻ ነው))*** (አል ማኢዳህ- 27)

ሶላት የማይሰግድ ሰው ጥንቁቅና ጌታውን ﷲ ን ፈሪ አይደለም።

ኢማሙ አሕመድ በዘገቡትና ቡረይዳ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦

« العهد الذى بيننا وبينهم الصلاة فمن تركها فقد كفر ».

*"በኛና በነርሱ (በከሃዲያን) መካከል ያለው ኪዳን ሶላት ነው፡፡ ሶላት የተወ ሰው በርግጥ ከኢስላም ወጥቷል፡፡"*

በሌላም ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

*« بَيْنَ الرَّجُلِ وَبَيْنَ الشِّرْكِ وَالْكُفْرِ تَرْكُ الصَّلاَةِ ».*

*"በአንድ ሰውና በክህደት መካከል ያለው ሶላትን መተው ነው፡፡"*

*"إجابة السائل على أهم المسائل" , "فقه العبادات"*

*ጥ5. የረመዳንን ወር መፆም ግዴታ የሚሆነው መቼ ነው?*

*መ. ግዴታ የሚሆነው የረመዳን ወር ጨረቃ መታየቱ ሲረጋገጥ፤* ካልታየ ደግሞ የሸዕባንን ወር ሰላሳ ቀን በመሙላት ይሆናል፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ዐብደላህ ቢን ዑመር رضي الله عنهما

ባስተላለፈው ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

« إِذَا رَأَيْتُمُوهُ فَصُومُوا وَإِذَا رَأَيْتُمُوهُ فَأَفْطِرُوا فَإِنْ غُمَّ عَلَيْكُمْ فَاقْدِرُوا لَهُ ».

*"(የረመዳን ጨረቃን) ስታዩ ፁሙ፡፡ (የሸዋልን ጨረቃ) ስታዩ ብሉ፡፡ (ጨረቃው) ከተሸፈነባችሁ ለርሱ ወስኑለት፡፡"*

በሌላም ዘገባ እንዲህ አሉ፡-

«فَصُومُوا لِرُؤْيَتِهِ وَأَفْطِرُوا لِرُؤْيَتِهِ فَإِنْ أُغْمِىَ عَلَيْكُمْ فَاقْدِرُوا لَهُ ثَلاَثِينَ»

*"(ጨረቃውን) ስታዩ ፁሙ፡፡ ስታዩት ብሉ፡፡ ከተሸፈነባችሁ ወሩን ሰላሳ ሙሉ፡፡"*

የዚህ አምሳያ ሐዲስ በአቡ-ሁረይራም رضي الله عنه ተዘግቧል፡፡

የነዚህ ሐዲሶች ጥቅል ሃሳብ :- (የረመዳንን) ጨረቃ ሳታዩ እንዳትፆሙ፣ (የሸዋልን) ጨረቃ ሳትመለከቱ የረመዳንን ወር ፆም እንዳታጠናቅቁ፣ የረመዳን ወር ጨረቃ ካልታያችሁ የሸዕባንን ወር ሰላሳ ቀን ሙሉት፣ የሸዋል ወር ጨረቃ ካልታያችሁ ደግሞ የረመዳንን ወር ሰላሳ ቀን ሙሉ ማለት ነው፡፡

"شرح مسلم"

***ጥ6.* የረመዳን ወር ጨረቃ በደመና በመሸፈኑ ምክንያት ካልታየ ማድረግ ያለብን ምንድን ነው?**

***መ.*** በኛ ላይ ግድ የሚሆነው ጥያቄ 4 ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በመመርኮዝ የሸዕባንን ወር ሰላሳ መሙላት ይሆናል፡፡

***ጥ7.* አጠራጣሪ የሆነን ቀን መፆም ፍርዱ ምንድን ነው?**

***መ.*** ይህን ቀን መፆም አይቻልም፡፡ ታላቁ ሰሓቢይ ዐማር ቢን ያሲር رضي الله عنهما እንዲህ ብሏል:-

**من صام اليوم الذى يشك فيه فقد عصى أبا القاسم**

***"ጥርጣሬ ያለበትን ቀን የፆመ በርግጥ የቃሲም አባትን አምፆኣል"*** ነብያችንን ﷺ ማለት ነው፡፡

"شرح مسلم", "المحلى" لابن حزم, "نيل الأوطار" للشوكاني

***ጥ8.* ከተለምዶ ውጭ ረመዳን አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው የሱና ፆም መፆም ፍርዱ ምንድን ነው?**

***መ.*** ረመዳን አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው መፃም አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና አቡ-ሁረይራ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

« لاَ تَقَدَّمُوا رَمَضَانَ بِصَوْمِ يَوْمٍ وَلاَ يَوْمَيْنِ إِلاَّ رَجُلٌ كَانَ يَصُومُ صَوْمًا فَلْيَصُمْهُ ».

***“ረመዳን አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው (ሱና) ፆም አትፁሙ፡፡ (ሱና) ፆም የመፆም ልምድ ያለው ሰው ግን ይፁም፡፡”***

-ኢማሙ አን-ነወዊይ (شرح مسلم)፣ ኢማሙ አስ-ሰንዓኒይ ( سبل السلام) በሚባለው ኪታባቸው ላይ ይህንን ሐሳብ አስቀምጠዋል፡፡

***ጥ9.*** ሱና ፆም የመፆም ልምድ ያለውና ይህ የሚፆምበት ቀን ረመዳን አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው የገጠመበት ከላይ ያለው ክልከላ ያካትተዋልን?

***መ.*** እንደዚህ አይነት ሰው ክልከላው አያካትተውም፡፡ ምክንያቱም የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ ከላይ በተጠቀሰው ሐዲስ ተለምዶ ያለው ሰው እንዲፆም ለይተው ፈቅደውለታል፡፡

***ጥ10.*** ከላይ ያለው ክልከላ ቀዷ ኖሮበት የሚፆምን ሰው ያካትታልን?

***መ.*** አያካትትም ምክንያቱም ቀዷ ግዴታ እንጂ ሱና አይደለም፡፡

***ጥ11.*** ከላይ ያለው ክልከላ የስለት ፆምን የሚፆም ሰው ያካትታልን?

***መ.*** አያካትትም ምክንያቱም ስለትን መሙላት ግዴታ ነው፡፡

-ረመዳን አንድና ሁለት ቀን ሲቀረው መፆም የተከለከለው ***"እንዳትፆሙ"*** የሚለው ክልከላ ሱና ፆም የመፆም ልምድ ያለውን ሰው፣ ቀዷ ያለበትንና የስለት ፆም የሚፆምን ሰው እንደማያካትት ብዙ ዑለማዎች ያስቀመጡት ሃሳብ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ኢብኑ ደቂቅ አልዒድ (إحكام الإحكام شرح عمدة الأحكام) ፣ ሐፊዝ ኢብኑ ሐጀር (فتح الباري) የተባሉ ኪታቦቻቸው ውስጥ አስቀምጠዋል፡፡

***ጥ12.*** የረመዳን ወር ጨረቃ እይታ ከሁሉም ሰው መገኘት አለበትን?

***መ.*** ሁሉም ሰው ጨረቃን ማየቱ በዑለማዎች ኢጅማዕ መሰረት መስፈርት አይደለም፡፡ ይልቁን ሐዲሱ የሚያመላክተው ሸሪዓዊ ፍርድ የሚፀናበት የአንድ ፍትሐዊ ሰው አሊያም የሁለት ሰው ምስክርነት በቂ ነው፡፡ (سبل السلام)

***ጥ13.*** የረመዳን ወር ጨረቃ ለመታየቱ የአንድ ሰው ምስክርነት በቂ ነውን?

***መ.*** አዎ! ይህም የአብዛኛው ዑለማዎች ሐሳብ ሲሆን ለዚህም ማስረጃው አቡ ዳውድ፣ ዳሪሚ፣ ኢብኑ ሒባን እና ሓኪም በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላ ቢን ዑመር رضي الله عنهما እንዲህ አሉ፡-

**تَرَاءَى النَّاسُ الْهِلاَلَ فَأَخْبَرْتُ رَسُولَ اللَّهِ -صلى الله عليه وسلم- أَنِّى رَأَيْتُهُ فَصَامَهُ وَأَمَرَ النَّاسَ بِصِيَامِهِ.**

***"ሰዎች ጨረቃን ለማየት ይቻኮሉ ጀመር፡፡ ከዚያም ለ الله መልዕክተኛ ﷺ እኔ ጨረቃን እንዳየኋት ነገርኳቸው፡፡ እርሳቸውም ፆመው ሰዎችንም እንዲፆሙ አዘዟቸው፡፡"***

ከዚህ ሐዲስ የምንማረው የ الله መልዕክተኛ ﷺ አንድ ፍትሐዊና ታማኝ ሰው ይዞላቸው በመጣው ዜና ተመርኩዘው ይህንን ፆም

መተግበራቸውን ነው። የአንድ ሰው ወሬ ነው ብለው ወሬውን አላጣጣሉበትም።

(شرح مسلم) (مجموع) (سبل السلام) (نيل الأوطار)

***ጥ14***. ***የአንድ አገር ሰዎች ጨረቃን ቢመለከቱ ለሌላ አገር ሰዎች መፆም ግድ ይላቸዋልን?***

***መ.*** አዎ የሚለው መልስ ትክክለኛው አቋም ሲሆን ለዚህ ማስረጃው የﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

« إِذَا رَأَيْتُمُوهُ فَصُومُوا

***"ጨረቃዋን ካያችሁ ፁሙ።"***

-ይህ ንግግር ቅርብም ሩቅም ያለውን ሁሉንም ህዝብ ያካትታል። ይህንን ሀሳብ ሸይኽ ኢብኑ ተይሚያ፣ ኢማሙ ሸውካኒ እና ኢማሙ አልባኒ ደግፈውታል።

(مجموع الفتاوى) (نيل الأوطار) (تمام المنة)

***ጥ15***. ***የረመዳንን ወር መፆም ግድ የሚሆነው በማን ላይ ነው?***

***መ.*** መፆም ግድ የሚሆነው በሚከተሉት ሰዎች ላይ ነው፡-

1. ሙስሊም፡- ሙስሊም ያልሆነ ሰው መጀመሪያ ሙስሊም መሆን አለበት ከዚያም እንዲያም ይደረጋል። ምክንያቱም ከሃዲ ስራው ተቀባይነት የለውምና።
2. አቅመ አዳም የደረሰና አዕምሮውም ጤነኛ መሆን፡-

አዕምሮው ጤነኛ ያልሆነ ሰው በመፆም አይገደድም። እንዲሁም አቅመ አዳም ያልደረሰ ሰውም መፆም ግድ አይሆንበትም። እነዚህ ሁለት አካላት ብዕር ተነስቶላቸዋል። ለዚህ ማስረጃው ኢማሙ አሕመድ፣ አቡ-ዳውድና ሓኪም

በዘገቡትና ዐብደላህ ቢን ዑመር رضي الله عنهما ባስተላለፈው ሐዲስ የ الله መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ:-

« رُفِعَ الْقَلَمُ عَنْ ثَلاَثَةٍ عَنِ الْمَجْنُونِ الْمَغْلُوبِ عَلَى عَقْلِهِ حَتَّى يُفِيقَ وَعَنِ النَّائِمِ حَتَّى يَسْتَيْقِظَ وَعَنِ الصَّبِيِّ حَتَّى يَحْتَلِمَ ».

*"ከሦስት ሰዎች ላይ ብዕር ተነስቷል፡፡ ከአዕምሮ ህመምተኛ እስኪፈወስ ድረስ፣ ከተኛ ሰው እስኪነቃ ድረስ እንዲሁም ከህፃን ላይ አቅመ አዳም እስኪደርስ"*

3. ለመፆም ችሎታ ያለው

ችሎታ የሌለው ሰው መፆም ግድ አይሆንበትም الله እንዲህ ይላል:-

﴿ لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا ﴾البقرة: ٢٨٦

**((الله አንዲትን ነፍስ ከአቅሟ በላይ አያስገድዳትም))** (አል-በቀራ 286)

4. በአገሩ ላይ ተቀማጭ የሆነ (መንገደኛ ያልሆነ) በመንገደኛና በህመምተኛ ዙሪያ الله እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ ﴾البقرة: ١٨٥

***((ከናንተ ውስጥ በጉዞ ላይ ወይም ህመምተኛ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (ቆጥሮ) ይፁም፡፡))*** *(አል-በቀራ 185)*

-በሐይድ (የወር አበባ ደም) እና በኒፋስ (የውልደት ደም) ላይ ያሉ ሴቶች በሌላ ጊዜ ያጠፉትን ያህል ይፆማሉ፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

« أَلَيْسَ إِذَا حَاضَتْ لَمْ تُصَلِّ ، وَلَمْ تَصُمْ .... » .

*"ሴት ልጅ የወር አበባ በመጣባት ጊዜ የማትሰግድና የማትፆም አይደለችምን ?"*

***ጥ16.*** ህፃናት እንዲፆሙ ይታዘዛሉን?

***መ.*** *መፆም የሚችሉ ከሆነ ማዘዙ ይወደደዳል፡፡ ምክንያቱም ፆምን እየተለማመዱ ያድጋሉ፡፡ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ ልጆች ሰባት አመት ሲሞላቸው በሶላት እንድናዛቸው፤ አስር አመት ሲሞላቸው ደግሞ ስገዱ ብለን እንድንገርፋቸው አመላክተውናል፡፡ ይህን የምናደርገው ከሰለፎች ብዙዎቹ እንዳሉት ግዴታ ሆኖባቸው ሳይሆን እንዲለማመዱ በማሰብ ነው፡፡*

***ጥ17.*** አንዲት ሴት የወር አበባዋ ከፈጅር በፊት ቢቋረጥና ከፈጅር በኃላ ብትታጠብ መፆም ግዴታ ይሆንባታልን?

***መ.*** *አዎ መፆም ግዴታ ይሆንባታል፡፡ ምክንያቱም እንዳትፆም የከለከላት ነገር ተቋርጧል፡፡ ከፈጅር በፊትም ሆነ በኃላ ብትታጠብ ችግር የለውም፡፡*(المحلى)

***ጥ18.*** ፆም ላይ ሆና ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የወር አበባዋ የመጣባት ሴት ምን ማድረግ አለባት?

***መ.*** *አንዲት ሴት ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት በደቂቃዎች ልዩነት የወር አበባ ከመጣባት ፆሟን አጥፍታ ቀዷ ማውጣት አለባት፡፡ ነገር ግን የወር አበባዋ የመምጣቱን ምልክት እንጂ ደም የፈሰሳት ከመግሪብ በኃላ ከሆነ ፆሟ ትክክል ነው፡፡*

"فـتـح الـبـاري", "فـقـه الـعـبـادات" لابـن عـثـيـمـيـن

***ጥ19.*** ***ለህመምተኛ መፆም ይፈቀድለታልን?***

***መ.*** መፆሙ ህመምተኛውን ጉዳት ላይ ካልጣለው፣ ህመሙን ካላባባሰበት ወይም ፈውሱን ካላዘገየበት መፆም ይችላል፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ አንዱን የሚያመጣበት ከሆነ እንዲበላ ተፈቅዶለታል፡፡

***ጥ20.*** ***የፀነሰች ሴት ልጅና ለነፍሷ የምትፈራ አጥቢ እናት በፆም ዙሪያ ፍርዳቸው ምንድን ነው?***

***መ.*** እነዚህ ሴቶች ይበሉና ካሉበት ሁኔታ ሲላቀቁ ቀዷ ያወጣሉ፡፡ ﷲ እንዲህ ይላል:-

﴿وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ﴾البقرة: ١٨٥

***((ከናንተ ውስጥ በጉዞ ላይ ወይም ህመምተኛ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (ቆጥሮ) ይፁም፡፡))*** *(አል-በቀራ 185)*

-እነዚህ ሴቶች ፍርዳቸው ከህመምተኛ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

(فـقـه الـعـبـادات)

***ጥ21.*** ***አንዲት ሴት በፆም ወቅት የወር አበባ መጥቶ በሌላ ጊዜ ቀዷ እንዳይኖርባት በማሰብ ይህንን ደም የሚያስቀር መድሐኒት መጠቀም ትችላለችን?***

***መ.*** ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን (ﷲ ይዘንላቸው) እንዲህ አሉ:- በዚህ ጉዳይ ላይ ያለኝ አመለካከት አንዲት ሴት ይህንን መድሐኒት መጠቀም እንደሌለባት ነው፡፡ ﷲ በወሰነውና በአደም ሴት ልጆች ላይ በፃፈው ህግ ላይ መፅናት ይኖርባታል፡፡ ﷲ

ይህንን የወር አበባ ያስገኘበት ከሴቶች ተፈጥሮ ጋር የሚገጥም ታላቅ ጥበብ አለው። አንዲት ሴት ይህንን ተፈጥሯዊ ደም እንዳይወጣ በምትከለክልበት ወቅት አካሏ (ሰውነቷ) ያለ ምንም ጥርጥር ጎጂ የሆነ ምላሽ ይኖረዋል።

የ الله መልዕክተኛ ﷺ አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ ባስተላለፈው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

« لاَ ضَرَرَ وَلاَ ضِرَارَ ».

*"መጉዳትም መጎዳዳትም የለም።"*

ይህንን የምንለው ይህን መድሐኒት ዶክተሮች በማህፀኗ ላይ ያመጣል ያሉትን ጉዳቶች ሳንመለከት ነው። (فقه العبادات)

***ጥ22.*** በእርጅና ምክንያት መፆም ያልቻለ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ፆሙን በመተው ይበላና ለእያንዳንዱ ቀን ምስኪንን ያበላል። ይህንን ሃሳብ ኢማሙል ቡኻሪ ከኢብኑ ዐባስ رضي الله عنهما በመያዝ አውስቷል። በተጨማሪም ይህንን ሃሳብ አብዛኛዎች ዑለማዎች ተናግረውታል።

***ጥ23.*** የመዳን ተስፋ የሌለው ህመምተኛ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህ ህመም እንዳይፆም የሚከለክለው ከሆነ ፍርዱ ችሎታ እንደሌለው ሰው ነው። (መፆም ግዴታ አይሆንበትም)

***ጥ24.*** ዘወትር መድሐኒት የሚጠቀምና ማቋረጥ የማይችል ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህ መድሐኒት በመርፌ የሚሰጥ ከሆነ ፆሙን ስለማያበላሽ እየፆመ መውሰድ ይችላል፡፡ ነገር ግን መድሐኒቱ የሚበላና የሚጠጣ ከሆነና ማቋረጥ የማይችል ከሆነ ፍርዱ እርጅና ላይ እንዳለ ሰው ይሆናል፡፡ ይህ ማለት እየበላ ለእያንዳንዱ ቀን ሚስኪን ያበላል፡፡

"فقه العبادات"

***ጥ25.*** እየፆመ በመርፌ መድሐኒትን የሚጠቀም ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህ መርፌ ምግብ ነክ ንጥረ ነገር ካለው ልክ እንደ መብላትና መጠጣት ስለሆነ ፆሙን ያጠፋበታል፡፡ መርፌው ምግብነት የሌለው መድሐኒት ከሆነ ግን መብላትና መጠጣት የሚለው ትርጓሜ ስለማይኖረው ፆሙ ትክክል ይሆናል፡፡

(فقه العبادات)

***ጥ26.*** አንዲት ሴት ፆመኛ ሆና ከተለምዶዋ ውጭ ደም ቢፈሳት ፍርዷ ምንድን ነው?

*መ.* ይህ ደም ከተለምዶ ውጭ ከሆነና የወር አበባ ደም እንዳልሆነ ከታወቀ ምንም ችግር አይፈጥርባትምና ፆሟን የመቀጠል ግዴታ አለባት፡፡ ምክንያቱም እንደ ነስር ዓይነት የደም እንጥብጣቢዎች የወር አበባ ደም አይደለም፡፡

***ጥ27.*** ፆመኛ ሆና ፅንስ ያስወረዳት ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?

***መ.*** የዚህች ሴት ፍርድ ልክ እንደ ውልደት ደም ሲሆን ይህ ደም እስኪቋረጥ ድረስ ትጠባበቃለች (አትፆምም) ይህ ያስወረዳት ፅንስ የተሟላም ይሁን ያልተሟላ ፍርዱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ﷲ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأُوْلَٰتُ ٱلۡأَحۡمَالِ أَجَلُهُنَّ أَن يَضَعۡنَ حَمۡلَهُنَّ ﴾الطلاق: ٤

*((የእርግዝና ባለቤቶች ጊዜያቸው ያረገዙትን መውለድ ነው::))* *(አል-ጦላቅ 4)*

ይህ የተሟላውንም ተሟልቶ ያልተፈጠረውንም ፅንስ ያካትታል፡፡ ይህ ፈትዋ የሸይኽ ሙቅቢል ፈትዋ ነው፡፡

***ጥ28.*** በረመዳን ወር ውስጥ ሆና የውልደት ደሟ ከአርባ ቀን በፊት የቆመላት ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህች ሴት ገላዋን ታጥባ መፆም ይኖርባታል፡፡ ምክንያቱም በውልደት ደም ምን ያህል ነው የሚቆየው ለሚለው ገደብ የለውም፡፡ (ابـن بـاز)

***ጥ29.*** የረመዳን ወር መፆም የሚጀምረው መቼ ነው?

***መ.*** መፆም የሚጀመረው እውነተኛው ጎህ ከቀደደ በኋላ ነው፡፡ الله እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَكُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكُمُ ٱلۡخَيۡطُ ٱلۡأَبۡيَضُ مِنَ ٱلۡخَيۡطِ ٱلۡأَسۡوَدِ مِنَ ٱلۡفَجۡرِ ﴾البقرة: ١٨٧

*((ከጎህ የሆነው ነጩ ክርም ከጥቁሩ ክር ለናንተ እስከሚገለፅላችሁ ድረስ ብሉ ጠጡም::))* *(አል-በቀራ 185)*

ኢማሙል ቡኻሪ በዘገቡትና ዓኢሻ رضي الله عنها ባስተላለፈችው ሐዲስ የ الله መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ፡-

« كُلُوا وَاشْرَبُوا حَتَّى يُؤَذِّنَ ابْنُ أُمِّ مَكْتُومٍ ، فَإِنَّهُ لاَ يُؤَذِّنُ حَتَّى يَطْلُعَ الْفَجْرُ » .

*"ኢብኑ ኡሚ መክቱም አዛን እስከሚል ድረስ ብሉ ጠጡ፡፡ እርሱ ጎህ ሲቀድ እንጂ አዛን አይልም፡፡"*

ጎህ ግልፅ ሆኖ ሲወጣ ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች መቆጠብ ግዴታ ይሆናል፡፡

***ጥ30.*** የእውነተኛው (ሁለተኛው) ጎህ ምልክት ምንድን ነው?

***መ.*** ምልክቱ በተራሮች አናት ላይ በአግድመት የሚሄድ ነው፡፡

የሶላትና የፆም ህግጋቶች የሚንጠለጠሉበት ጎህ ይሄኛው ነው፡፡ ኢማሙ ሙስሊም በዘገቡትና ሰሙራ ቢን ጁንዱብ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ፡-

« لاَ يَغُرَّنَّكُمْ مِنْ سَحُورِكُمْ أَذَانُ بِلاَلٍ وَلاَ بَيَاضُ الأُفُقِ الْمُسْتَطِيلُ هَكَذَا حَتَّى يَسْتَطِيرَ هَكَذَا ».يعني: معترضا

*"የቢላል አዛን ወይም የአድማሱ እንደዚህ መንጣት ከሱሑራችሁ እንዳያግዳችሁ እንደዚህ (በአግድመት) እስኪሆን ድረስ"*

***ጥ31.*** ለጥንቃቄ ተብሎ ጎህ ሳይቀድ የፈጅርን አዛን ማቻኮል ይቻላልን?

***መ.*** አይቻልም፡፡ ሓፊዝ ኢብኑ ሐጀር "فتح الباري" በተሰኘው ኪታባቸው ውስጥ ይህንን ተግባር የተወገዘ ቢድዓ (መጤ) ተግባር ብለውታል፡፡ አንድ ሙአዚን ሰዎች እምነት የጣሉበት አካል ነውና

ﷲ እንዲበሉና እንዲጠጡ በፈቀደላቸው ወቅት እርሱ መብላትና መጠጣትን ክልክል ሊያደርግባቸው አይገባም፡፡

ኢማሙል ሓኪም እንዲሁም በይሀቂይ በዘገቡትና ጃቢር رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ፡-

**الفجر فجران فأما الفجر الذي يكون كذنب السرحان فلا يحل الصلاة ولا يحرم الطعام وأما الذي يذهب مستطيلا في الأفق فأنه يحل الصلاة ويحرم الطعام.**

***"ጎህ ሁለት (አይነት) ነው፡፡ ያ ልክ እንደ ተኩላ ጅራት የሚሆነው ጎህ የሶላት ወቅት መግባቱንም አያመላክትም፤ ምግብንም ክልክል አያደርግም፡፡ ያ በአድማሱ ላይ ረዝሞ የሚሄደው ጎህ ግን ምግብን ሲከለክል የሶላት ወቅት መግባቱንም ያመላክታል፡፡"***

***ጥ32.*** የፈጅርን የመጀመሪያ አዛን በመተው በቁርኣንና በተለያዩ ዚክሮች መቀየር ይቻላልን?

***መ.*** ዑለማዎች እንዲህ ብለዋል፡- "ይህ ተግባር በዲን ውስጥ አዲስ የመጣ ቢድዓና ከነብያችን ﷺ መንገድ ያፈነገጠ ነው፡፡ እርሳቸው ﷺ በርግጥ እንዲህ ብለዋል፡-

**«فَمَنْ رَغِبَ عَنْ سُنَّتِي فَلَيْسَ مِنِّي».**

***"ከኔ መንገድ የሸሸ ከኔ አይደለም"***

በሌላም ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ዓኢሻ رضي الله عنها ባስተላለፈችው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

« مَنْ أَحْدَثَ فِي أَمْرِنَا هَذَا مَا لَيْسَ مِنْهُ فَهُوَ رَدٌّ »

*“በዚህ በዲናችን ውስጥ ከርሱ ያልሆነን አዲስ ነገር ያመጣ እርሱ ተመላሽ ነው::”*

***ጥ33.*** ገና ሌሊት ነው ብሎ ከበላና ከጠጣ በኃላ ጎህ የቀደደ መሆኑን ያወቀ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** አብዛኛው ዑለማዎች የዚህ ሰው ፆም ትክክል ነው ቀዷ የለበትም ብለዋል:: ﷲ እንዲህ ይላል:-

﴿ وَلَيۡسَ عَلَيۡكُمۡ جُنَاحٞ فِيمَآ أَخۡطَأۡتُم بِهِۦ ﴾الأحزاب: ٥

*((በተሳሳታችሁበትም ነገር ላይ ሐጢያት የለባችሁም))* *(አል-አሕዛብ 5)*

ኢማሙ ጠበራኒ በዘገቡትና ሠውባን رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛﷺ እንዲህ ብለዋል:-

" رُفِعَ عن أمَّتي الخَطأ والنِسيَانُ وما اسْتكْرِهُوا عليْهِ " .

*“ከህዝቦቼ ላይ ባለማወቅ የተሳሳቱትን፣ በመርሳት የፈፀሙትንና ተገደው የሰሩትን ሥራ (ወንጀሉ) ተነስቶላቸዋል:: (አይጠየቁበትም)”*

*"إجابة السائل عن أهم المسائل" ,"فقه العبادات"*

***ጥ34.*** ከፈጅር ሁለተኛ አዛን በኃላ የሚጠጣ ነገርን የጠጣ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ሙአዚኑ ጎህ ሳይቀድ ነው አዛን ያለው ብሎ የወቅቱን አለመግባት እርግጠኛ ካልሆነ በስተቀር ጎህ ከቀደደ በኃላ መብላትም መጠጣትም አይችልም::

ምክንያቱም ﷲ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَكُلُوا۟ وَٱشْرَبُوا۟ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكُمُ ٱلْخَيْطُ ٱلْأَبْيَضُ مِنَ ٱلْخَيْطِ ٱلْأَسْوَدِ مِنَ ٱلْفَجْرِ ﴾البقرة: ١٨٧

***((ከጎህ የሆነው ነጩ ክር ከጥቁሩ ክር ለናንተ እስኪገለፅላችሁ ድረስ ብሉ ጠጡ፡፡))*** *(አል-በቀራ 185)*

*"ያ በእጁ ላይ እቃው እንዳለ አዛን የሰማ ሰው ፍላጎቱን እስኪፈፅም እንዳያስቀምጠው"* የሚለው ሐዲስ ኢማሙ አሕመድ፣ ሓኪምና አቡ ዳውድ ከአቡ-ሁረይራ رضي الله عنه በመያዝ የዘገቡት ሐዲስ ሲሆን በሰነዱ ላይ ችግር ስላለ ለማስረጃነት አይበቃም፡፡

***ጥ35.*** ጀናባ ሆኖ ፈጅር የደረሰበት ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህ ሰው ገላውን ታጥቦ ፆሙን ይቀጥላል ቀዷ የለበትም፡፡ የጀናባው ምክንያት በኢሕቲላም (በእንቅልፍ ላይ የዘር ፈሳሽ መፍሰስ) ወይም የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞም ቢሆን ያው ነው፡፡ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ ከሚስቶቻቸው ጋር ግንኙነት በመፈፀም ጀናባ ሆነው ፈጅር ሲደርስባቸው ይታጠቡና ፆማቸውን ይቀጥሉ ነበር፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና የአማኞች እናት የሆኑት ዓኢሻና ኡሙ ሰለማ رضي الله عنهما ባስተላለፉት ሐዲስ የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል:-

« وَأَنَا تُدْرِكُنِي الصَّلاَةُ وَأَنَا جُنُبٌ فَأَصُومُ ».

***"እኔ ጀናባ ላይ ሆኜ ሶላት ይደርስብኛል ከዚያም ፆሜን እቀጥላለሁ፡፡"***

***ጥ36.*** የጀናባን ትጥበት ሆን ብሎ ጎህ እስኪቀድ ድረስ ማዘግየት ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** አንድ ሰው ሆን ብሎም ይሁን ረስቶ ቢያዘገይ ፆሙ አይበላሽም፡፡ ግዴታ የሚሆንበት መታጠብ ብቻ ነው፡፡

"فتح الباري"

***ጥ37.*** በረመዳን ወር በቀኑ ክፍለ ጊዜ ኢሕቲላም የሆነ (በእንቅልፉ ሳለ የዘር ፈሳሽ የፈሰሰው ሰው) ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ፆሙ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን ገላውን መታጠብ ይኖርበታል፡፡

***ጥ38.*** ሱሑር መብላት ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ሱሑር መብላት የተወደደ ተግባር ነው፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና አነስ ኢብኑ ማሊክ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ የ الله መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

« تَسَحَّرُوا فَإِنَّ فِي السَّحُورِ بَرَكَةً » .

*"ሱሑርን ብሉ፡፡ ሱሑርን መብላት በረከት አለው፡፡"*

በሌላም ሙስሊም በዘገበውና ዐምር ኢብኑል ዓስ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

« فَصْلُ مَا بَيْنَ صِيَامِنَا وَصِيَامِ أَهْلِ الْكِتَابِ أَكْلَةُ السَّحَرِ ».

*"በኛና በመፅሐፍት ባለቤቶች ፆም መካከል ያለው ልዩነት ሱሑርን መብላት ነው፡፡"*

ሱሑርን መብላት የተወደደ በመሆኑ ላይ የዑለማዎች ስምምነት እንዳለ ኢማሙ ነወዊ (شرح مسلم) ላይ አውስተዋል፡፡

***ጥ39.*** ሱሑርን መመገብ በረከት አለው ለምን ተባለ?

***መ.*** ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- ነብያችንንﷺ መታዘዝና የርሳቸውን ሱና (መንገድ) መከተል ስለሆነ
- ነብያችንﷺ ተቃረኗቸው ያሉንን ከሃዲያንን መቃረን ስለሆነ
- በቀን ክፍለ ጊዜ በአምልኮት ላይ እንድንበረታታ ስለሚያግዘን
- ፆመኛውን ንቁ ሆኖ እንዲውል ስለሚያስችለው
- ሁሌም ፆምን በመፆም ላይ ፍላጎት እንዲኖረን ያደርጋል
- በሱሑር ወቅት ሶደቃ እንድንሰጥ ምክንያት ይሆናል
- በሱሑር ወቅት ﷲን እንድናወሳ ምክንያት ይሆናል
- ፆመኛው ለፆሙ ኒያ እንዲያደርግ ምክንያት ይሆናል

  ሌሎችም ያልተጠቀሱ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡
  "شرح مسلم", "فتح الباري"

***ጥ40.*** አንድ ሰው ሱሑር ተጠቅሟል ለመባል ምን ያህል መመገብ አለበት?

***መ.*** በአንድ አፍ የሚጨልጠው ትንሽ ውሃ በቂ ነው፡፡ አቡ-ሁረይራ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ነብያችን ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

( تسحروا ولو بجرعة من ماء )

***"እንዴ በምትጎነጨት ውሃም ቢሆን ሱሑርን ተመገቡ።"***

አቡ ዳውድና ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል

***ጥ41.*** **የተሻለ ጥሩ ሱሑር የሚባለው ምንድን ነው?**

***መ.*** **አቡ-ሁረይራ** رضي الله عنه **ባስተላለፈው ሐዲስ ነብያችን** صلى الله عليه وسلم **ይህንን መልስ ሲመልሱ እንዲህ አሉ፡-**

**« نعم سحور المؤمن التمر ».**

***"የሚያምረው የሙእሚን ሱሑር ቴምር ነው።"*** አቡ ዳውድና ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል

***ጥ42.*** **ሱሑር ምሳ ተብሎ ይጠራልን?**

***መ.*** **አዎ! ይባላል። ምክንያቱም የ** ﷲ **መልዕክተኛ** ﷺ **ሱሑርን ምሳ ብለው ጠርተውታል። ዒርባድ ቢን ሳሪያህ** رضي الله عنه **እንዲህ ይላል "የ** ﷲ **መልዕክተኛ** ﷺ **በረመዳን ወር ለሱሑር ጠሩኝና እንዲህ አሉኝ፡-**

**« هلم إلى الغداء المبارك »**

***"ወደ ተባረከው ምሳ ና"*** አቡዳውድ፣ ነሳኢ፣ ኢብኑ ኹዘይማና ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል

***ጥ43.*** **ሱሑርን ለፈጅር ትንሽ ደቂቃ እስኪቀረው ድረስ ማዘግየት እንዴት ይታያል?**

***መ.*** **የተወደደ ሱና ነው። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ይህንን ሱና ችላ ብለዋል አንዳንዶችማ እኩለ ሌሊት ላይ ተነስተው ጠግበው በመብላት ይተኙና የፈጅር ሶላት ያመልጣቸዋል። የነብያችን** ﷺ **ተለምዶ ግን ሱሑርን ፈጅር ትንሽ ሲቀረው መብላት ነበር።**

ያ *"ህዝቦቼ ሱሑርን ካዘገዩና አፍጥርን ካፋጠኑ ከመልካም ሁኔታ አይወገዱም"* የሚለው ሐዲስ ግን ለማስረጃነት የማይበቃ (ደዒፍ) ነው። ምክንያቱም በሰነዱ ውስጥ "ሱለይማን ቢን አቢ ዑስማን" የሚባል ሰው አለ። አቡ-ሓቲም ይህንን ሰው የማይታወቅ (መጅሁል) ብሎታል። ነገር ግን ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡትና ሰህል ቢን ሰዕድ رضي الله عنه ያስተላለፈው:-

***"ሰዎች አፍጥርን እስካፋጠኑ ድረስ ከመልካም አይወገዱም"*** **የሚለው ሐዲስ ትክክለኛ ነው።**

***ጥ44.*** ሱሑርን ሳይመገብ የፆመ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ፆሙ ትክክል ነው ነገር ግን የሱሑር ምንዳና በረከት አምልጦታል።

***ጥ45.*** በረመዳን በቀኑ ክፍለ ጊዜ ያለምንም ምክንያት የበላ ወይም የጠጣ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህ ሰው በጣም ትልቅ ወንጀል ላይ ወድቋልና በሰራው ትልቅ ሓጢኣት መፀፀትና ተውበት ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል።

ነገር ግን *"ከረመዳን ወር አንድ ቀን ያለምንም ምክንያትና ህመም ያጠፋ ሰው የአመት ፆም ቢፆም እንኳ አያካክሰውም"* የሚለው ሐዲስ ለማስረጃነት የማይበቃ ደዒፍ ሐዲስ ነው።

***ጥ46.*** ከላይ ባለው ጥያቄ ላይ ትንሽ የበላና ብዙ የበላ ልዩነት አለውን?

***መ.*** ምንም ልዩነት የለውም።

***ጥ47.*** ፆመኛ መሆኑን ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰው ፍርዱስ ምንድን ነው?

***መ.*** ፆሙ ትክክል ነው ቀዷም የለበትም።

ﷲ አማኞች እንዲህ ይላሉ ብሏል፡-

﴿ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَآ إِن نَّسِينَآ أَوْ أَخْطَأْنَا ﴾البقرة: ٢٨٦

*((ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንሳሳት አትያዘን (አትቅጣን)፡፡))*
*(አል-በቀራ 286)*

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና አቡ ሁረይራ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ነብያችን ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

« مَنْ نَسِيَ وَهُوَ صَائِمٌ فَأَكَلَ أَوْ شَرِبَ فَلْيُتِمَّ صَوْمَهُ فَإِنَّمَا أَطْعَمَهُ اللَّهُ وَسَقَاهُ ».

*“ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰው ያበላውና ያጠጣው ﷲ ነውና ፆሙን ይቀጥል፡፡”*

***ጥ48.*** በረመዳን በቀኑ ክፍለ ጊዜ ፆመኛ ሆኖ ከሚስቱ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ይህ ሰው ፆሙን ያበላሸበትን ትልቅ ወንጀል ፈፅሟል ስለዚህ ከፋራ (ማካካሻ) ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል፡፡ (شرح مسلم)

***ጥ49.*** ማድረግ ያለበት ከፋራ (ማካካሻ) ምንድን ነው?

***መ.*** አማኝ የሆነን ባሪያ ነፃ ማውጣት፤ ይህንን ለማድረግ አቅም ከሌለው ሁለት ወር በተከታታይ ይፆማል፣ ይህም ካቃተው ስድሳ ድሆችን ያበላል፡፡ ይህንን ፍርድ የሚያመላክተው ሐዲስ ከታላቁ ሰሓቢይ አቡ ሑረይራ رضي الله عنه በመያዝ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

***ጥ50.*** ከፋራ (ማካካሻ) ማድረግ ያልቻለ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ከፋራውን ከናካቴው መፈፀም ያልቻለ ሰው ከአቅሙ በላይ አይገደድምና ይወድቅለታል፡፡ ﷲ እንዲህ ይላል፡-

﴿لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا﴾البقرة: ٢٨٦

***((ﷲ አንዲት ነፍስን ከአቅሟ በላይ አያስገድዳትም))*** *(አል-በቀራ 286)*

-ወደ ፊት አቅም አግኝቶ ማካካሻውን ማድረግ ከቻለ ማድረጉ ግዴታ ይሆንበታል፡፡

***ጥ51.*** ባሏ የተገናኛት ሴት ይህ ከፋራ (ማካካሻ) ግዴታ ይሆንባታልን?

***መ.*** ግዴታ አይሆንባትም ምክንያቱም በረመዳን ግንኙነት የፈፀመው ሰውዬ ነብያችን ﷺ ጋር በመጣ ጊዜ እርሱ ላይ እንጂ እርሷ ላይ ግድ አላደረጉባትም፡፡

***ጥ52.*** በረመዳን ቀን ከሚስቱ ጋር ግንኙነት ከፈፀመ በኋላ በዚያው ቀን ጉዞ የወጣ ወይም የታመመ ሰው ይህ ከፋራ (ማካካሻ) ይሰረዝለታልን?

***መ.*** አይሰረዝለትም ምክንያቱም ዑዝሩ የመጣው ከግንኙነቱ በኋላ ነው፡፡

"فقه العبادات"لابن عثيمين

***ጥ53.*** ባሏ አስገድዷት ግንኙነት የፈፀመች ሴት ፍርዷ ምንድን ነው?

***መ.*** ፆሟ ትክክል ነው (አይፈርስም) ከፋራም ግድ አይሆንባትም፡፡

"فقه العبادات"

***ጥ54.*** ከፋራው (ማካካሻው) ድሆችን ማብላት የሆነ ሰው ሁሉንም በአንድ ላይ በአንድ ቀን ማብላት ግድ ይሆንበታልን?

***መ.*** ግድ አይሆንበትም፣ መስፈርትም አይደለም፡፡

لابن حزم "المحلى"

***ጥ55.*** ከፋራ (ማካካሻ) ያለበት ሰው የሰላሳ ሰውን ምግብ ለአንድ ሰው መመገብ ይችላልን?

***መ.*** ይህንን ማድረግ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሰላሳ ሰዎችን ሁለት ሁለት ጊዜ መመገብ አይችልም፡፡ ማድረግ ያለበት ወንድም ይሁን ሴት ስድሳ ለሆኑ ድሆች መመገብ ነው፡፡

(المحلى)

***ጥ56.*** በዚህ ከፋራ (ማካካሻ) ማጥገብ ግዴታ ነውን?

***መ.*** አዎ! ከከፋራው መስፈርቶች ውስጥ ማጥገብ አለበት የሚለው ይገኝበታል፡፡

(المحلى)

***ጥ57.*** በዚህ ከፋራ (ማካካሻ) ቴምርን የመሰለ አንድ አይነት ምግብን ማድረግ ይችላልን ?

***መ.*** አዎ ይችላል (ያብቃቃዋል)፡፡

"المحلى"

***ጥ58.*** ፆመኛ ሆኖ ሚስቱን የተገናኘ ነገር ግን የዘር ፈሳሽ ያልፈሰሰው ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** በዚህ ሰው ላይ የ48ኛው ጥያቄ መልስ ያካትተዋል፡፡

***ጥ59.*** በረመዳን ፆም በቀኑ ክፍለ ጊዜ በአንድ ቀን ውስጥ ሚስቱን ደጋግሞ የተገናኘ ሰው ስንት ከፋራ አለበት?

***መ.*** ይህም ሰው ከላይ በተጠቀሰው መልኩ አንዴ ከፋራ ያወጣል፡፡

***ጥ60.*** ከረመዳን ቀናቶች ውስጥ ሁለት ቀን ሚስቱን የተገናኘ ስንት ከፋራ አለበት?

***መ.*** በዚህ ሰው ላይ ለያንዳንዱ ቀን ራሱን የቻለ ከፋራ ያወጣል፡፡

"المحلى"

***ጥ61.*** በአውሮፕላን ጉዞ የሚያደርግ ሰው ፆሙን አፍርሶ መብላት ይችላልን?

***መ.*** መጓጓዣው ቢለያይም መንገደኛ ነውና الله በቁርኣን ውስጥ ፆሙን ማጥፋት እንደሚችል ተናግሯል፡፡

***ጥ62.*** ጉዞን ለማድረግ ቁርጠኛ የሆነ ሃሳብ ያለው ሰው ከሃገሩ ከመውጣቱ በፊት መብላት ወይም መጠጣት ይችላልን?

***መ.*** ለጥንቃቄ የበለጠውና የተሻለው ከሃገሩ እስኪወጣ አለመብላት ነው፡፡

***ጥ63.*** በጉዞ ላይ ላለ መንገደኛ የተሻለው መፆም ነው ወይስ ማፍጠር?

***መ.*** የተሻለው የቀለለውን መምረጥ ነው፡፡

***ጥ64.*** በረመዳንም ሆነ በሌላ ጊዜ ዘወትር ጉዞ ላይ የሚሆን ሰው ያለው ፍርድ ምንድን ነው?

*መ.* ረመዳን ላይ መንገደኛ ሆኖ መፆም ከቻለ ይፆማል ካልቻለ ግን ፆሙን አጥፍቶ በሚችል ጊዜ ቀዷ ያወጣል፡፡

***ጥ65.*** *ፆመኛ የሆነ ሰው ዋግምት መደረግ ይችላልን?*

*መ.* ፆሙን ለማፍረስ ምክንያት እስካልሆነው ድረስ ይችላል፡፡ ቡኻሪ በዘገበውና ኢብኑ ዐባስ رضي الله عنهما ባስተላለፈው ሐዲስ የ الله መልዕክተኛ ﷺ ፆመኛ ሆነው ዋግምት ተደርገዋል፡፡

(الفتح) (زاد المعاد)

-ያ *"ዋግምት አድራጊውም ተደራጊውም ፆማቸው ተበላሽቷል"* የሚለው ሐዲስ (ህጉ) የተሻረ ሐዲስ ነው፡፡

(75-72\4 الإرواء )

***ጥ66.*** *አንድ ፆመኛ ሚስቱን ቢስማት ፆሙን ያበላሽበታልን?*

*መ.* መሳም በራሱ ፆምን አያፈርስም ወደ ሐራም እስካላመራ ድረስ ይችላል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ውስጥ በተዘገበው ሐዲስ እንደተረጋገጠው ነብያችን ﷺ ፆመኛ ሆነው ሚስቶቻቸውን ይስሙ ነበር፡፡

"فتح الباري"

***ጥ67.*** *ፆመኛ የሆነ ሰው መፋቂያ መጠቀም ይችላልን?*

*መ.* አዎ ይችላል፡፡ የ الله መልዕክተኛ ﷺ ውዱእ ሲያደርጉ፣ ሶላት ሲሰግዱ እና ቤታቸው ሲገቡ መፋቂያን ይጠቀሙ ነበር፡፡ እንዲሁም ፆመኛንም ይሁን ሌላውን ሰው ከዙሁር በፊትም ይሁን በኋላ መፋቂያን በመጠቀም ላይ አነሳስተዋል፡፡

فتح الباري

***ጥ68. ፆመኛ የሆነ ሰው የጥርስ ሳሙናን መጠቀም ይችላልን?***

***መ. አዎ ወደ ጉሮሮ እስካልደረሰ ድረስ መጠቀም ይችላል፡፡***

***ጥ69. ፆመኛ ሆኖ ውዱ ሲያደርግ ውሃ ወደ ሆዱ የገባበት ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?***

***መ. ሆን ብሎ እስካላስገባ ድረስ ፆሙ ትክክል ነው አይበላሽበትም፡፡ በ47ኛው ጥያቄ መልስ ላይ እንደተቀመጠው አዛኙ ጌታችን ﷲ እኛ ተሳስተን፣ ረስተንና ተገደን በምንሰራው ይቅር ብሎናል፡፡***

**(فتح الباري)        (فقه العبادات)**

***ጥ70. አንድ ፆመኛ እራሱን ለማቀዝቀዝ ብሎ ፀጉሩን መታጠብ ይችላልን?***

***መ. አዎ! ምክንያቱም ነብያችን ﷺ ፆመኛ ሆነው ሲጠማቸውና ሙቀቱ ሲበረታባቸው ፀጉራቸው ላይ ውሃ ያፈሱ ነበር፡፡*** (አሕመድና አቡ ዳውድ)

***ሐሰን አል-በስሪ እንዲህ ይላል፡- "አንድ ፆመኛ መጉመጥመጥም ራሱንም ማቀዝቀዝ ይችላል፡፡"*** ኢማሙል ቡኻሪ አውስቶታል

***ጥ71. ፆመኛ የሆነ ሰው በቀን ከአንዴ በላይ ገላውን መታጠብ ይችላልን?***

***መ. አዎ! ይችላል፡፡ (የሚከለክል ማስረጃ የለም)***

**"فقه العبادات"**

***ጥ72. ዐይንን ኩል መኳል ፆምን ያበላሻልን?***

***መ. አብዛኞዎቹ ዑለማዎች ፆምን እንደማያበላሽ ተናግረዋል፡፡***

"الفتح"

ሐሰነል በስሪ እንዲህ አለ፡- ፆመኛ ሰው ቢኳል ችግር የለውም።

"مصنف عبد الرزاق"

***ጥ73.*** የዐይን፣ የጆሮ ወይም የአፍንጫ ጠብታ ፆም ያበላሻልን?

***መ.*** ጣዕም ቢሰማውም እንኳ ፆምን አያበላሽም።

"حقيقة الصيام" لابن تيمية, "زاد المعاد"

***ጥ74.*** ፆመኛ የሆነ ሰው በሚተነፍስ ጊዜ የሚገባበት አቧራና ጭስ ፆምን ያበላሻልን?

***መ.*** አያበላሸበትም። ልክ እንደዚሁ እንደ ዝንብ ያሉ ነፍሳቶች ቢገቡበት ፆሙን አያበላሸበትም።

"فتح الباري"

***ጥ75.*** ምራቅን መዋጥ ፆምን ያበላሻልን?

***መ.*** ዐጧዕ ቢን አቢ ረባሕና ቀታዳ እንዲህ ይላሉ፡- ፆመኛ ሰው ምራቁን ቢውጥ ችግር የለውም።

"فتح الباري"

***ጥ76.*** አክታን መዋጥ ፆም ያበላሻልን?

***መ.*** ፆምን አያበላሽም ነገር ግን ጀርሞችን የተሸከመ ቆሻሻ ነውና ፆመኛም ሆነ ሌላ ሰው መዋጡ የተጠላ ነው።

***ጥ77.*** ማስታወክ ፆምን ያበላሻልን?

***መ.*** ያበላሻል የሚል ማስረጃ የለም። ነገር ግን ያስመለሰውን ምግብ ሆን ብሎ የዋጠ ፆሙ ይበላሻል።

***ጥ78.*** *ማቀርሸት ፆምን ያበላሻልን?*

***መ.*** ቅርሻት ፆምን አያበላሽም፡፡ ነገር ግን ያቀረሸ ሰው አፍ ላይ ያለውን ወደ ውጭ የመትፋት ግዴታ አለበት፡፡ ወደ ሆድ ማስገባት የለበትም፡፡

***ጥ79.*** አንድ ፆመኛ ፆሙን የሚፈታው (የሚያፈጥረው) መቼ ነው?

***መ.*** የ الله መልዕክተኛﷺ ዑመር رضى الله عنه በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ፡-

« إِذَا أَقْبَلَ اللَّيْلُ مِنْ هَا هُنَا ، وَأَدْبَرَ النَّهَارُ مِنْ هَا هُنَا ، وَغَرَبَتِ الشَّمْسُ ، فَقَدْ أَفْطَرَ الصَّائِمُ » .

***"ሌሊቱ ከዚህ በኩል (በምስራቅ) ከመጣ፣ ቀኑ ደግሞ ከዚህ በኩል (ከምዕራብ) ከመጣ ፀሐይም ከጠለቀች በእርግጥ ፆመኛ ፆሙን ፈትቷል፡፡"***

-ይህ ሐዲስ ፆም ፀሐይ በመጥለቋ ብቻ እንደሚፈታና አፍጥርን ማቻኮል እንደሚወደድ ያስተምረናል፡፡

"شرح مسلم"

***ጥ80.*** አፍጥርን ማፍጠን ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** ሌሊቱ መግባቱና ፀሐይ መጥለቋ ከተረጋገጠ አፍጥርን ማቻኮል የተወደደ ሱና ነው፡፡ የዚህ ኡማ በመልካም ሁኔታ የመቀጠሉ ምልክትም ነው፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ሰህል ኢብኑ ሰዕድ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ነብያችን ﷺ እንዲህ ብለዋል:-

**« لاَ يَزَالُ النَّاسُ بِخَيْرٍ مَا عَجَّلُوا الْفِطْرَ ».**

***"ሰዎች ፋጡርን በማፍጠናቸው ከመልካም ሁኔታ አይወገዱም።"***

-ኢማሙ ነወዊ ስለዚህ ሐዲስ ሃሳብ እንዲህ አሉ:- *"እነዚህ የረሱል ﷺ ህዝቦች ይህንን ሱና ይዘው እስከዘወተሩ ድረስ በመልካም ሥርዓት ላይ ከመሆን አይወገዱም። በተቃራኒው ማፍጠርን ካዘገዩ የወደቁበትን የተበላሸ ሁኔታ ያመላክታል።"*

"شرح مسلم"

-ኢብኑ ደቂቅ አል-ዒድ እንዲህ አሉ:- *"ይህ ሐዲስ ኮከቦች ብቅ እስኪሉ ድረስ አፍጥርን የሚያዘገዩትን ሺዓዎች የሚያወግዝ ሲሆን ሰዎች ፋጡርን እስካፈጠኑ ድረስ ከመልካም ሁኔታ አይወገዱም የተባለውም ለዚህ ነው። ምክንያቱም ፋጡርን ሲያዘገዩ የነብያችንን ﷺ መንገድ ይቃረናል። ሱናን እስከተገበሩ ድረስ ግን ከመልካም ተግባር አይወገዱም።"*

"إحكام الإحكام"

***ጥ81.*** ኮከቦች እስኪታዩ ድረስ አፍጥርን ማዘግየት ፍርዱ ምንድን ነው?

***መ.*** የ الله መልዕክተኛ ﷺ ሰህል ቢን ሰዕድ رضي الله عنه ባወራው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል:-

**( لا تزال أمتي على سنتي ما لم تنتظر بفطرها النجوم )**

***"የኔ ህዝቦች ፆማቸውን ለማፍጠር ኮከቦችን እስካልተጠባበቁ ድረስ ከኔ መንገድ አይወገዱም"***

**በሌላም አቡ-ሁረይራ** رضي الله عنه **ባወራው ዘገባ እንዲህ አሉ፡-**

**لاَ يَزَالُ الدِّينُ ظَاهِرًا مَا عَجَّلَ النَّاسُ الْفِطْرَ ، إِنَّ الْيَهُودَ وَالنَّصَارَى يُؤَخِّرُونَ.**

***"ይህ ሐይማኖት ሰዎች አፍጥርን እስካፈጠኑ ድረስ የበላይ ከመሆን አይወገድም። ምክንያቱም አይሁድና ክርስቲያኖች አፍጥራቸውን ያዘገያሉና።"***

-በዚህ ሐዲስ መሰረት አፍጥርን ማዘግየት የነብያችንን صلى الله عليه وسلم መንገድ መቃረን ይሆናል። በተጨማሪም አፍጥርን ማዘግየት የአይሁዶችና የክርስቲያኖች መንገድ ነውና የኡማውን መበላሸት ያመላክታል። ሐፊዝ ኢብኑ ሐጀር አፍጥርን ማዘግየት ከተወገዘ ቢድዓ (ፈጠራ) ውስጥ ነው በማለት ፅፏል።

"فتح الباري"

***ጥ82.*** አፍጥርን መብላት የተወደደው ከመግሪብ በፊት ነው ወይስ ከመግሪብ በኋላ?

***መ.*** አነስ ኢብኑ ማሊክ رضي الله عنه እንዲህ ይላል፡-

**ما رأيت النبي صلى الله عليه و سلم قط صلى المغرب حتى يفطر ولو على شربة من ماء.**

***"የﷲ መልዕክተኛን ﷺ ትንሽ ውሃን በመጠጣትም ቢሆን ሳያፈጥሩ መግሪብ ሶላትን ሰግደው አይቼ አላውቅም::"***

***ጥ83.*** *ፆመኛ* ሰው የሚያፈጥረው በምንድን ነው?

***መ.*** እርሱ በወደደውና በፈለገው ምግብ ማፍጠር ይችላል፡፡

-*ያ "ነብያችንﷺ ከመስገዳቸው በፊት በሩጦቦች ያፈጥሩ ነበር፤ ሩጦብ ከሌላቸው በቴምሮች፤ቴምርም ከሌላቸው በውሃ ያፈጥሩ ነበር"* የሚለው ሐዲስ ደዒፍ (ደካማ) ነው አይሰራበትም፡፡

-ኢማሙ ዘሃቢይ እንዲህ ብለዋል፡- "ይህ ሐዲስ በሰነዱ ላይ ያለው ጃዕፈር ኢብኑ ሱለይማን የሚባለው ዘጋቢ ላይ የተወገዘበት ሐዲስ ነው፡፡

***ጥ84.*** አንድ *ፆመኛ* ሲያፈጥር የሚለው ዱዓ ምንድን ነው?

***መ.*** በዚህ ቦታ የመጣ ለየት ያለ ዱዓ የለም፡፡

-*ያ "ጥማቱ ተወገደ፣ ጅማቶችም ራሱ፣ ምንዳውም በ ﷲ ፍቃድ ፀና"* የሚለው ሐዲስ በሰነዱ ውስጥ "መርዋን ኢብኑ ሳሊም" ስላለ እርሱም መጅሁል (የማይታወቅ) ስለሆነ ሐዲሱ ደዒፍ ነው፡፡

***ጥ85.*** *ፆመኛን* ማስፈጠር ያለው አጅር ምንድን ነው?

***መ.*** ምንም ጥርጥር በሌለው ሁኔታ አጅር አለው፡፡ ዘይድ ኢብኑ ኻሊድ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ነብያችን صلى الله عليه وسلم እንዲህ ብለዋል፡-

« مَنْ فَطَّرَ صَائِمًا كَانَ لَهُ مِثْلُ أَجْرِهِ غَيْرَ أَنَّهُ لاَ يَنْقُصُ مِنْ أَجْرِ الصَّائِمِ شَيْئًا ».

*“ፆመኛን ያስፈጠረ ሰው ከፆመኛው አጅር ሳይቀነስ ልክ እንደ ፆመኛው አጅር ይኖረዋል*:: ቲርሚዚ፣ አሕመድ ኢብኑ ማጃህ ኢብኑ ሒባን

***ጥ86.*** አንድ ፆመኛ ተጋብዞ ካፈጠረ በኃላ ለጋባዡ የሚያደርገው ዱዓ ምን ቢሆን ይመረጣል?

***መ.*** ይህንን ከነብያችን ﷺ የተገኘ ዱዓ ቢጠቀም ይወደዳል፡-

" أَكَلَ طَعَامَكُمُ الْأَبْرَارُ وَأَفْطَرَ عِنْدَكُمُ الصَّائِمُونَ وَصَلَّتْ عَلَيْكُمُ الْمَلَائِكَةُ "

*“ምግባችሁን መልካም ሰዎች ይብሉ፣ መላእክቶች ዱዓ ያድርጉላችሁ፣ ፆመኞች እናንተ ዘንድ ያፍጥሩ::”*

-ሸይኽ አልባኒ እንዲህ አሉ፡- “ይህ ዱዓ ፆመኛ ብቻ ተጋብዞ ካፈጠረ በኃላ የሚያደርገው ዱዓ ሳይሆን ሁሉም ሰው በየትኛውም ወቅት ለጋባዡ የሚያደርገው ዱዓ ነው::

-በሐዲሱ መጨረሻ ላይ ﷲ *እርሱ ዘንድ ያሉት ፉጡሮች ጋር ያስታውሳችሁ”* የሚለው ጭማሪ ትክክል ያልሆነ ጭማሪ ነው::

***ጥ87.*** ዊሳል (*ፆምን መቀጣጠል*) ትርጉሙና ፍርዱ ምንድን ነው?

*መ.* ዊሳል ማለት አንድ ፆመኛ ፆሙን በመሃል ሳያፈጥር ሁለትና ከዚያ በላይ ቀናቶችን መፆም ማለት ነው። ነብያችን ﷺ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ይህንን ተግባር ከልክለዋል።

-ኢማሙል ኸጣቢና ሌሎችም እንዲህ አሉ፡- "ዊሳል ለነብያችን ﷺ ብቻ የተፈቀደና ለሌሎች ሰዎች የተከለከለ ተግባር ነው።"

"شرح مسلم"

***ጥ88.*** እስከ ሱሑር ወቅት ሳያፈጥሩ ፆምን መቀጠል ፍርዱ ምንድን ነው?

*መ.* ችግር የለውም፡፤ ነብያችን ﷺ አቡ ሰዒድ رضي الله عنه ባወራው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

«لا تواصلوا ، فأيُّكم أرادَ أن يُوَاصِلَ فليُواصِلْ حتى السحَرِ.

***"ፆምን አትቀጣጥሉ። መቀጠል የፈለገ ሳያፈጥር እስከ ሱሑር ድረስ ብቻ ይቀጥል።"***

***ጥ89.*** በረመዳን ሌሊት የመስገድ ትሩፋት ምንድን ነው?

*መ.* ነብያችን ﷺ አቡ-ሁረይራ ባወራው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

« مَنْ قَامَ رَمَضَانَ إِيمَانًا وَاحْتِسَابًا غُفِرَ لَهُ مَا تَقَدَّمَ مِنْ ذَنْبِهِ » .

***"የረመዳንን ሶላት አምኖበትና ምንዳውን እየተሳሰበ ለሶላት የቆመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ይማርለታል።"***

***ጥ90.*** የረመዳንን የሌሊት ሶላት በአንድ ላይ መስጂድ ውስጥ ተሰባስቦ መስገድ ይቻላልን?

***መ.*** አዎ! ይቻላል፡፡ ነብያችን ﷺ እንዲህ በማለት አነሳስተዋል፡-

**إِنَّ الرَّجُلَ إِذَا صَلَّى مَعَ الْإِمَامِ حَتَّى يَنْصَرِفَ حُسِبَ لَهُ قِيَامُ لَيْلَةٍ**

***"አንድ ሰው ኢማሙ እስኪጨርስ አብሮ ከሰገደ ሌሊቱን ሙሉ እንደሰገደ ይቆጠርለታል፡፡"***

-ነብያችን ﷺ ሶሓቦችን ሰብስበው ያሰግዱ ነበር ከዚያም ግዴታ እንዳትደረግ ሰግተው ተውት፡፡ (ቡኻሪ)

-ዑመር ኢብኑል ኸጣብ رضي الله عنه ሶሓቦች ተበታትነው ለየብቻ ሲሰግዱ አይቶ ኡበይ ኢብኑ ከዕብን رضي الله عنه ኢማም በማድረግ አንድ ላይ እንዲሰግዱ አድርጓቸዋል፡፡ (ቡኻሪ ዘግቦታል ፈትሑል ባሪን ተመልከት)

***ጥ91.*** የሌሊት ሶላት የሚሰገደው ስንት ረከዓ ነው?

***መ.*** የﷲ መልዕክተኛ ﷺ ከአስራ አንድ ረከዓ በላይ ጨምረው አያውቁም፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ እናታችን ዓኢሻ رضي الله عنها እንዲህ ትላለች፡-

**مَا كَانَ رَسُولُ اللَّهِ - صلى الله عليه وسلم - يَزِيدُ فِى رَمَضَانَ وَلاَ فِى غَيْرِهِ عَلَى إِحْدَى عَشْرَةَ رَكْعَةً**

***"የﷲ መልዕክተኛ ﷺ በረመዳንም ይሁን ከረመዳን ውጭ ከአስራ አንድ ረከዓ በላይ ጨምረው አያውቁም፡፡"***

-በተጨማሪም የኢማሙ ማሊክ "موطأ" ውስጥ እንደተዘገበው ዑመር ኢብኑል ኸጧብ رضي الله عنه ኡበይ ኢብኑ ከዕብን رضي الله عنه አስራ አንድ ረከዓ እንዲያሰግድ አዞታል፡፡

***ጥ92.*** የሌሊት ሶላት እየሰገደ የደከመው ሰው ቁጭ ብሎ መስገድ ይችላልን?

***መ.*** አዎን! የሱና ሶላቶች ላይ አንድ ሰው መቆም እየቻለም ቁጭ ብሎ መስገድ ይችላል፡፡ ይህ ሐሳብ ዑለማዎች የተስማሙበት ነው፡፡

ኢማሙል ቡኻሪ በዘገበው ሐዲስ ዒምራን ኢብኑ ሑሰይን رضي الله عنه እንዲህ አለ፡- የ መልዕክተኛን ቁጭ ብሎ ስለሚሰግድ ሰው ጠየቅኳቸው እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

« مَنْ صَلَّى قَائِمًا فَهْوَ أَفْضَلُ ، وَمَنْ صَلَّى قَاعِدًا فَلَهُ نِصْفُ أَجْرِ الْقَائِمِ ، وَمَنْ صَلَّى نَائِمًا فَلَهُ نِصْفُ أَجْرِ الْقَاعِدِ » .

***“ቆሞ የሰገደ እርሱ የተሻለ ነው፡፡ ቁጭ ብሎ የሚሰግድ ሰው ቆሞ ከሚሰግደው ሰው አጅር ግማሹን ያገኛል፡፡ ተኝቶ የሚሰግድ ቁጭ ብሎ ከሚሰግደው ሰው አጅር ግማሹን ያገኛል፡፡”***

*ኢማሙል ቡኻሪ እንደዘገበው ነብያችን ﷺ የለይልን ሶላት ቆመውም ቁጭ ብለውም ይሰግዱ ነበር፡፡*

***ጥ93.*** ቁጭ የሚለው ሰጋጅ እንዴት ነው የሚሰግደው?

***መ.*** በፈለገው መልኩ መስገድ ይችላል፡፡

***ጥ94.*** በረመዳን የሌሊት ሶላት ቁኑት ማድረግ ይቻላልን?

*መ.* አዎን! ነብያችን ﷺ ሐሰን ኢብኑ ዐሊ,ይን رضي الله عنهما ቁኑት ዱዓ ሲያደርግ ይህንን በማለት አስተምረውታል፡- አቡ ዳውድ፣ ነሳኢና ሌሎችም ዘግበውታል፡፡

**« اللَّهُمَّ اهْدِنِي فِيمَنْ هَدَيْتَ وَعَافِنِي فِيمَنْ عَافَيْتَ وَتَوَلَّنِي فِيمَنْ تَوَلَّيْتَ وَبَارِكْ لِي فِيمَا أَعْطَيْتَ وَقِنِي شَرَّ مَا قَضَيْتَ إِنَّكَ تَقْضِي وَلاَ يُقْضَى عَلَيْكَ وَإِنَّهُ لاَ يَذِلُّ مَنْ وَالَيْتَ وَلاَ يَعِزُّ مَنْ عَادَيْتَ تَبَارَكْتَ رَبَّنَا وَتَعَالَيْتَ ».**

***"ﷲ ሆይ! ቀናውን መንገድ እንደመራሃቸው ሰዎች እኔንም ምራኝ፣ይቅር እንዳልካቸው ሰዎች እኔንም ይቅር በለኝ፣አንተ ረዳት እንደሆንካቸው ሰዎች እኔንም እርዳኝ፤ በለገስከኝ ነገር ሁሉ በረከቱን አድርግልኝ፣ ከወሰንከው መጥፎ ነገርም ጠብቀኝ፣ አንተ ወሳኝ ነህ ባንተ ላይ የሚወሰን የለም፤ አንተ ረዳት የሆንከው ሰው አይዋረድም፣ አንተ ጠላት ያደረግከው የበላይ አይሆንም፤ ጌታችን ሆይ! አንተ ረድዔተ ብዙና የተላቅክ ነህ፡፡"***

***ጥ95.*** ከላይ ከተጠቀሰው ዱዓ ውጭ መጨመር ይቻላልን?

*መ.* አዎን! ይህ ጉዳይ ከሰለፎች (ከቀደምቶች) ተገኝቷል፡፡

"قيام الليل" للألباني

***ጥ96.*** ይህ ቁኑት የሚደረገው ከሩኩዕ በፊት ነው ወይስ በኃላ?

*መ.* ከሶሓቦች በመገኘቱ በሁለቱም ማድረግ ይቻላል፡፡

"قيام الليل" للألباني

***ጥ97.*** **ዊትር ሶላትን ስንጨርስ የሚባል ዚክር አለን?**

***መ.*** አዎን! የተወደደ ዚክር አለ። ነብያችን ﷺ ዊትርን ሲጨርሱ ይህንን ዱዓ ይሉ ነበር፡-

**« سُبْحَانَ الْمَلِكِ الْقُدُّوسِ ».**

***"ብፁዕ የሆነው ጌታ ከጉድለት የጠራ ነው"***

ነገር ግን

**« سُبُّوحٌ قُدُّوسٌ رَبُّ الْمَلاَئِكَةِ وَالرُّوحِ ».**

የሚለው ጭማሪ ደዒፍ ነው።

***ጥ98.*** **ለይለተል ቀድር የሚሆነው መቼ ነው?**

***መ.*** ነብያችን ﷺ እንደነገሩን በረመዳን የመጨረሻ አስር ቀናቶች ውስጥ ነጠላ የሆኑት ናቸው። ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ዓኢሻ رضي الله عنها ባስተላለፈችው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

**« تَحَرَّوْا لَيْلَةَ الْقَدْرِ فِي الْوِتْرِ مِنَ الْعَشْرِ الأَوَاخِرِ مِنْ رَمَضَانَ » .**

***"ለይለተል ቀድርን በመጨረሻዎቹ አስር ነጠላ ቀናቶች ውስጥ ፈልጓት"***

-በአብዛኛው የረመዳን 27ኛው ቀን ነው። ሙዓዊያ رضي الله عنه ባስተላለፈው ሐዲስ ነብያችን ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

**« لَيْلَةُ الْقَدْرِ لَيْلَةُ سَبْعٍ وَعِشْرِينَ ».**

*“ለይለቱል ቀድር 27ኛው ሌሊት ነው”*

-ኡበይ ኢብኑ ከዕብም رضي الله عنه እንዲህ ብሏል:-

وَاللَّهِ الَّذِى لاَ إِلَهَ إِلاَّ هُوَ إِنَّهَا لَفِى رَمَضَانَ - يَحْلِفُ مَا يَسْتَثْنِى - وَوَاللَّهِ إِنِّى لأَعْلَمُ أَىُّ لَيْلَةٍ هِىَ. هِىَ اللَّيْلَةُ الَّتِى أَمَرَنَا بِهَا رَسُولُ اللَّهِ -صلى الله عليه وسلم- بِقِيَامِهَا هِىَ لَيْلَةُ صَبِيحَةِ سَبْعٍ وَعِشْرِينَ وَأَمَارَتُهَا أَنْ تَطْلُعَ الشَّمْسُ فِى صَبِيحَةِ يَوْمِهَا بَيْضَاءَ لاَ شُعَاعَ لَهَا.

***“በﷲ እምላለሁ (ለይለቱል ቀድር) የትኛዋ ሌሊት እንደሆነች አውቃለሁ እርሷም ነብያችን ﷺ ሌሊቷን (በሶላት) እንድንቆመው ያዘዙን ሌሊት ስትሆን ይህቺ ሌሊት 27ኛዋ ናት። ከምልክቶቿ ውስጥ በዚያው ቀን በማለዳ የምትወጣው ፀሐይ ቀለል ያለችና ጨረር የሌላት ትሆናለች።”***

***ጥ99.*** ሌሊቱ ለይለተል ቀድር ለመሆኑ ምልክት ምንድን ነው?

***መ.*** ኢብኑ ዐባስ رضي الله عنه እንደሚለው ምልክቱ ከላይ እንደተቀመጠው ፀሐይ ነጣ ብላ ጨረር አልባ ከመሆኗ በተጨማሪ የሌሊቱ አየር የተረጋጋ (ብርዳማም ሞቃታማም ያልሆነ መካከለኛ) ይሆናል።

***ጥ100.*** የተከለከሉ ምስሎችንና ሙዚቃን ማዳመጥ የፆምን ምንዳ ይቀንሳልን?

***መ.*** ሸይኽ ኢብኑ ዑሰይሚን እንዲህ ይላሉ:-

*“ወደ ተከለከለ (ሐራም) ነገሮች መመልከትና መስማት ያለጥርጣሬ በፆም ላይ ተፅዕኖ አለው አጅሩንም ይቀንሳል፡፡ ምክንያቱም ፆም የተደነገገበት ዋና አላማ ተቅዋን (ﷲን መፍራት) ለማስገኘት ነው፡፡ ”*

ﷲ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣ ﴾البقرة: ١٨٣

***((እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፆም ከናንተ በፊት በነበሩት ላይ እንደተፃፈው በናንተ ላይም ተደነገገ፡፡ ልትጠነቀቁና ልትፈሩ ይከጀላልና፡፡))***

-ﷲ  በዚህ አንቀፅ ላይ ግልፅ እንዳደረገው የፆም ድንጋጌ ሚስጥር እርሱን መፍራት ነው፡፡ ቡኻሪ በዘገበው ሐዲስ ነብያችን ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

**عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ عَنِ النَّبِيِّ - صلى الله عليه وسلم - قَالَ « مَنْ لَمْ يَدَعْ قَوْلَ الزُّورِ وَالْعَمَلَ بِهِ وَالْجَهْلَ فَلَيْسَ لِلَّهِ حَاجَةٌ أَنْ يَدَعَ طَعَامَهُ وَشَرَابَهُ » .**

***“(ፆመኛ ሆኖ) የውሸት ንግግርንና በርሱም መስራትን እንዲሁም መሃይምነትን ያልተወ ምግብና መጠጥን ስለተወ ለ ﷲ ጉዳይ የለውም”***

*"فقه العبادات"*

# ዘካተል-ፊጥራችንን በታዘዝነው መልኩ እናውጣ

## ካሊድ ጠይብ

*ምስጋና ለ ﷲ የተገባ ነው፡፡ ሶላትና ሰላም በ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ እንዲሁም በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እነርሱን በመልካም በተከተለ ላይ ይሁን!*

*በዚህች ትንሽ ወረቀት ላይ ስለ ዘካተል ፊጥር ማብራሪያና ዑለማዎች በዚህ ርዕስ ዙሪያ የሰጡትን ፈትዋ ሰብስበናል ረጋ ባለ መንፈስ በማንበብ በተግባር ላይ እንድናውል ﷲ ይርዳን!*

- ***ዘካተል ፊጥር ተብሎ የተሰየመው ለምንድን ነው?***

*-ኢብኑ ቁዳማ "المغني" በተባለው ኪታቡ ቅፅ 3 ገፅ 55 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ይህ ዘካ ወደ ፊጥር የተጠጋው (ዘካተል ፊጥር የተባለው) ይህንን ዘካ መስጠት ግድ የሚሆነው በረመዳን ማፍጠሪያ (ዒድ) ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡"*

- ***ዘካተል ፊጥር የተደነገገው መቼ ነው?***

*-ሸይኽ በሳም "نيل المأرب" በሚባለው ኪታቡ ቅፅ 2 ገፅ 389 ላይ እንዲህ ይላል፡- "ዘካተል ፊጥር የተደነገገው የረመዳን ፆም በተደነገገበት አመት በሁለተኛው አመተ ሂጅራ ነው፡፡"*

- ***ዘካተል ፊጥር የተደነገገበት ምክንያት ምንድን ነው?***

*-አቡ-ዳውድ፣ ኢብኑ-ማጃህና ሓኪም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ እንዲህ በማለት አስተላልፏል፡- "የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ ፆመኛን ከተናገራቸው መጥፎ ንግግሮችና ተግባሮች ያነፃው ዘንድ እንዲሁም ለሚስኪኖች ምግብ እንዲሆን ዘካተል ፊጥርን ደነገጉ…"*

- ***ዘካተል ፊጥር ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?***

*ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ይላል፡- “የ ﷲ **መልዕክተኛ ﷺ በወንድና በሴት፣ ባሪያ ባልሆነና ባሪያ በሆነ፣ ትንሽም ትልቅም በሆነ ሙስሊም ላይ ሰደቀቱል ፊጥርን ግድ አደረጉ።”***

*በዚህ ሐዲስ መሰረት ማንኛወም ሙስሊም ለራሱና በርሱ ውስጥ ላሉት ማለትም ለሚስቱ፣ ለልጆቹ፣ ለኻዲሞቹና ሌሎች በርሱ ስር ላሉ ሰዎች ማውጣት አለበት። ነገር ግን ከአብዛኛው ዑለማዎች እንደተገኘውና ኢብኑል-ሙንዚር ኢጅማዕ እንደዘገበው በፅንስ ውስጥ ላለ ልጅ ዘካተል ፊጥር የለበትም (ግድ አይሆንበትም)።*

- ***ዘካተል ፊጥር መስጠት ግዴታ የሚሆነው መቼ ነው?***

*ይህ ዘካ ግዴታ የሚሆነው በረመዳን መጨረሻ ላይ የዒድ ጠዋት ፈጅር ሲወጣ ነው።*

*ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ይላል፡- “የ ﷲ መልዕክተኛ ﷺ **ዘካተል ፊጥር ሰዎች ወደ ዒድ ሶላት ከመውጣታቸው በፊት እንዲሰጥ አዘዙን።”***

*እንዲሁም ከኢማሙ አሕመድና ከኢማሙ ማሊክ እንደተገኘውና አብዛኛው ዑለማዎች እንዳሉት ዘካተል ፊጥር ረመዳን ከማለቁ በአንድ ወይም በሁለት ቀን አስቀድሞ ማውጣት ይቻላል።*

- ***አንድ ሰው ግድ የሚሆንበት የዘካተል ፊጥር መጠን ምን ያህል ነው?***

*ዘካተል ፊጥር የሚሰጠው ከምግብ ሲሆን ልኩም አንድ ሷዕ ነው። አንድ ሷዕ ደግሞ ልኩ መካከለኛ የሆነ ሰው አራት እፍኝ ነው። ይህም ወደ ኪሎ ሲቀየር ሁለት ኪሎ ከግማሽ ይቃረባል። በዚህ ልክ ከስንዴ፣ ከቴምር ወይም ከዘቢብ ባጠቃላይ መልኩ አንድ ሰው ካለበት ሀገር በአብዛኛው ከሚመገቡት ምግብ በተጠቀሰው*

*ልክ ያወጣል። ይህ ልክ ለአንድ ሰው ሲሆን ብዙ ቤተሰብ ያለው ኃላፊ በቤተሰቦቹ ቁጥር ልክ የተጠቀሰውን መጠን አስቦ ያወጣል።*

- ***ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ ማውጣት ይቻላልን*** ?

*ዝንባሌዎቻቸውን የሚከተሉ የአስተያት ሰዎች ከላይ የተጠቀሰውን የእህል መጠን በገንዘብ ቀይሮ መስጠት ይቻላል በማለት አብዛኛውን ሙስሊም እያሳሳቱ ነው። በዚህ ዙሪያ የተሰጠውን የዑለማዎች ፈትዋ እናንብብ፦*

*-ኢብኑ ቁዳማ "المغني" በሚባለው ኪታቡ ላይ እንዲህ ይላል፦ "የዘካተል ፊጥር ልኩን በገንዘብ የሰጠ ሰው አያብቃቃውም።"*

*-ኢማሙ ነወዊ በ 984ኛው ሐዲስ ላይ እንዲህ ይላል፦ "ሁሉም የዲን ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች የዘካተል ፊጥርን መጠን በገንዘብ መስጠት አያብቃቃም ብለዋል።"*

*-ሸይኽ ኢብኑ ባዝ እንዲህ ይላሉ፦ "...በርግጥ ብዙ ሰዎች ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ መስጠት ፍርዱ ምንድን ነው ብለው ጠይቀውኛል መልሱ እንደሚከተለው ነው፤ በማንኛውም ትንሽ አዕምሮ ባለው ሙስሊም ላይ "شهادة أن لا إله إلا الله" የሚያስፈርደው ከﷲ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለ፣ شهادة أن محمدا رسول الله ደግሞ የሚያስፈርደው መልዕክተኛው ﷺ በደነገጉት መንገድ እንጂ ﷲ ላይመለክ መሆኑ አይደበቅበትም። ዘካተል ፊጥር ደግሞ ሙስሊሞች ባጠቃላይ እንደተስማሙበት አምልኮ ነው። ማንኛውም ሰው ደግሞ ምንም ማስረጃ ሳይኖረው አምልኮት ማድረግ አይችልም። ﷲ ስለ መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ይላል፦*

﴿ وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلۡهَوَىٰٓ ۝٣ إِنۡ هُوَ إِلَّا وَحۡيٞ يُوحَىٰ ۝٤ ﴾النجم: ٣ -

*(( ከልብ ወለድ አይናገርም ከእርሱ (ንግግር) የሚወርድ ራዕይ ቢሆን እንጂ ሌላ አይደለም፡፡))*

*የﷲ መልዕክተኛ ﷺ ደግሞ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡትና ዓኢሻ ባስተላለፈችው ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-*

***"በዚህ ዲናችን ላይ ከርሱ (ከዲኑ) ያልሆነን ነገር የፈጠረ እርሱ (ፈጠራው) ተመላሽ ነው፡፡"** በኢማሙ ሙስሊም ዘገባ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡-*

***"የኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ስራ የሰራ እርሱ (ስራው) ተመላሽ ነው፡፡"***

*የﷲ መልዕክተኛ ﷺ ሶሒሕ ሆነው በመጡ ሐዲሶች እንደተረጋገጠው ዘካተል ፊጥር አንድ ሷዕ ቴምር ፣ወይም አንድ ሷዕ ስንዴ ወይም ደግሞ አንድ ሷዕ ከዘቢብ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ እንግዲህ በዘካተል ፊጥር በኩል ያለው የመልዕክተኛው መንገድ ይህ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ደግሞዘ ዘካተል ፊጥር በተደነገገበት ወቅት በሙስሊሙ ህብረተሰብ ውስጥ በተለይ መዲና ውስጥ የዲናርና የዲርሀም ገንዘቦች ነበሩ፡፡ ነገር ግን በገንዘብ እንዲሰጡ አልታዘዙም፡፡ ከሶሓቦችም በገንዘብ ሰጠ የተባለ አይታወቅም ቢኖር ደግሞ ይዘገብልን ነበር፡፡ ﷲ እንዲህ ይላል፡-*

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ ﴾الأحزاب: ٢١

***((በእርግጥ በﷲ መልዕክተኛ ላይ መልካም መከተል አላችሁ))***

*እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱ ማስረጃዎች መሰረት እውነትን ለያዘ ሰው ዘካተል ፊጥርን በገንዘብ (በብር) ማውጣት እንደማይቻልና ላወጣውም ሰው እንደማያብቃቃው ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሰውን ማስረጃ የሚቃረን በመሆኑ፡፡*

*ምንጭ:- (مجموع الفتاوى لابن باز ቅፅ 14 ገፅ 208-211)*

*-ከሸይኽ ኢብኑ ባዝ በተጨማሪ ሸይኽ ኢብኑ ዑሰይሚን፣ ሸይኽ ሙቅቢል፣ ሸይኻችን ያሕያና ሌሎችም እውቀታቸውን በተግባር ላይ የሚያውሉ ሰለፊይ ዐሊሞች ዘካተል ፊጥር በገንዘብ (በብር) መስጠት እንደማያብቃቃ ተናግረዋል። ስለዚህ ከቁርኣንና ከሐዲስ የመነጨውን ይህን መንገድ በመከተል ዘካተል ፊጥራችንን ከላይ ከተጠቀሱት ምግቦች ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው መጠን ማውጣት አለብን። እንዲሁም ስሜታቸውን በመከተል ቁርኣንንና ሐዲስን ከሚቃረኑ ሰዎች መንገድ በመጠንቀቅ እራሳችንን ከኪሳራ ማዳን አለብን።*

*ﷲ ይወፍቀን*

# ምስጋና

በመጀመሪያ ሁሌም ረዳቴ ለሆነው ጌታዬ ምስጋናዬን አደርሳለሁ

ቀጥዬም በዲኔ እንድፀና ለምታግዘኝ ለባለቤቴና የልጆቼ እናት ለሆነችው ሰዐዳ አብደላ መልካም ምንዳዋን ይለግሳት ዕድሜዋንም በመልካም ስራ ያርዝምላት

እንዲሁም የፅሁፍ ስራዬ የተሳካ እንዲሆን ሁሌም ከጎኔ ለማይጠፋው ኑርሁሴን ዳውድ ﷲ ምንዳውን ያብዛለት